ምዕራፍ ፫
ግስ

ፍሥሓ ጓዴ ተስፈው

፳ ፻ ፲ ፬ ዓ.ም

ደብረ ታቦር፥ ኢትዮጵያ

ግሥ ብሒል ምንት ብሒል ውእቱ? (ግስ ማለት ምን ማለት ነው?)

- ግሥ የሚለው ቃል ጌሰ ከሚለው ግስ የወጣ ነው።
- ገ(ጌ)ሠ/ገሥገሠ ማለትም ገሰገሰ፣ቸኮለ፣አረበደ፣ ፈጠነ ገሰሰ(ገሲስ፤ ገሰ ገሰሰ) ፣ዳሰሰ፣መረመረ ማለት ነው።
- ገሰሰ =በአብይና በንዑስ፣በሩቅና በቅርብ፣በወንድና በሴት ዘረዘረ

ግሥ ማለት ቀለም አገሥጋሽ ማለት ነው ፤ ምክንያቱም ማንኛውም አረፍተ ነገር ያለ ግሥ የማይነገር የማይገሠግሥም ነውና ፤ ዕርባታው ሁሉ ሲወርድ ግሥ ወረደ ይባላል ።

የግዕዝ ትምህርት መጀመሪያው ግሥ ይባላል ፤ ቅኔ ከመቍጠሩ በፊት ግሥ መግሠሥ ማውረድ ነው ፤ ስለዚህ የግዕዝ ትምህርት ሁሉ ግሥ ለማለት ግዕዝ ተብ ሏል ። ብዙዎች ሊቃውንት እንደሚሉት የሆነ እንደሆነ ግን ግሥ ማለት ግዕዝ ካለው ቃል የተወረሰ እንደሆነ ይናገራሉ ።

የቀጠለ…

- የማድረግንና የመሆንን ስሜት የሚገልጽ ቃል ነው፡- ስለዚህ ግሥ ማለት የቃላት ምእላድ ወይም መገኛ ማለት ነው።
- ግሥ ማሰሪያ አንቀጽነት ወይም የድርጊት ገላጭነት ሚና አለው።
- በአማርኛ ግስ የአረፍተ ነገር መቋጫ ነው።

ሰዋስው

- በግእዝ ቋንቋ ውስጥ ከሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ሰፊውን ቦታ የሚይዘው የሰዋስው ክፍሉ ነው።
- ሰዋስው ተብሎ በአንድ ቃል ይነበባል። መሰላልና መሸጋገሪያ ተብሎ በሁለት ቃል ይፈታል።
- ሰዋስው ስለምን መሰላል ተባለ ቢሉ በመሰላል ከታች ወደ ላይ ይወጡበታል።ከላይም ወደ ታች ይወርዱበታል።
- በሰዋስውም በእግረ ሕሊና ሰማየ ሰማያት ወጥቶ ዕመቀ ዕመቃት ወርዶ በዓይነ ልቡና ምሥጢረ ሥላሴን ያዩበታል።
- መሸጋገሪያ ያለው ስለምን ነው ቢሉ በመሸጋገሪያ ከወዲህ ወዲያ፤ ከወዲያ ወዲህ ይመላለሱበታል፤ይሸጋገሩበታል።
- በሰዋስውም በእግረ ልቡና እምጽማዌ ውስጠ ጥበብ፤እምኢያእምሮ ውስተ አእምሮ ይመላለሱበታል።

<u>የግሥ ስልት</u>

- ለአጠናን ይረዳን ዘንድ ግሶችን **በአራት** ክፍላት ከፍለን እንመለከታቸዋለን።

<u>፩</u>, <u>**ገቢር ግሥ፡-**</u> ይህ የግሥ ዐይነት ቃላትንና ሐረጋትን መሳብ የሚችል የአድራጊ ድርጊት የሚገለጽበት የግሥ ዓይነት ነው። በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሁልጊዜ ገቢር ስሞችን ይወስዳል። (ባለቤቱ ምን ሰራ ?)

- ምሳሌ፡-ገብረ =ሠራ ፣ ዘገበ= ሰበሰበ ፣ አርኀወ = ከፈተ፣ ፈኀረ አጨ ፣ ወዘተ…
- አብርሃም **ገብረ** ምግ<u>ብረ</u> ሠናይ
- በቀዳሚ **ገብረ** እግዚአብሔር <u>ሰማየ ወምድረ</u>

፫. <u>**ተገብሮ ግሥ፡-**</u> ይህ የግሥ ዓይነት በገቢር ግሥ ላይ ባዕድ ፊደል "ተ"ን በመነሻ በመጨመር የሚመሠረት ሲሆን የተደራጊ ድርጊትን ይገልጻል። ይህ የግሥ ዓይነት ገቢር ቃላትን አትስብም።ምሳሌ፡-

<u>ገቢር</u>	<u>ተገብሮ</u>
• ገብረ	ተገብረ
• ዘገበ	ተዘግበ
• ሤመ	ተሤመ…

ማስታወሻ፡-

- በ"ተ" የሚጀምር ግሥ ሁሉ ተገብሮ ግሥ አይደለም።
  - ምሳሌ፡- ተንበለ/ለመነ፣ ተሞገሰ/ባለሟል ሆነ፣ ተምዐ/ተቆጣ፣ ተመነየ/ተመኘ፣ ወዘተ
- በ"**ተ**" የሚጀምር ግሥ **ተገብሮ** የሚሆነው '**ተ**'ን አስወግደን የተቀረው **ገቢር ግሥ** በመሆን ትርጉም ካለው ብቻ ነው።

፫. ነባር አንቀጽ፤ አደረገ ወይም ተደረገ የማይሉ "መኖር/አለመኖር፣ መሆን/አለመሆን"ን የሚገልጹ፡ አይነታቸው እና ቁጥራቸውም እንደ ገቢር ተገብሮ የተልዩ ና የማይበዙ ናቸው።

- ውእቱ=ነው፣ ነበረ፣አለ፣ ኖረ
- ቦ= አለ፣ ኖረ፣ ነበረ
- አኮ=አይደለም፣
- አልቦ=የለም፣ አልኖረም፣ አልነበረም
- አሆ= እሺ
- ሎ/ሎቱ= አለው፣ ነበረው፣ ነበረው
- እዎ=አዎ
- ሀሰ=አይደለም
- ሀሎ= አለ፣ ኖረ፣ ነበረ፣ ይኖራል፣ ይኑር
- ኢ = አፍራሽ

- ከገቢርና ከተገብሮ ግሦች የሚለዩበትና የሚመሳሰሉበት ሁኔታ አለ።

- **የሚለያዩበት፡-**

1, መድረሻ ፊደሉ ካእብና ሳብዕ መሆኑ
2, በካልዓይ፣ በዘንድና በትዕዛዝ አንቀጽ አለመገኘታቸው
3, ከንዑስ አንቀጽ እስከ ቦዝ አንቀጽ ድረስ ያሉትን እርባታዎች አለማካተቱ

- **የሚያመሳስላቸው፡-**

1, ማሰሪያ አንቀጽ መሆን መቻላቸው እና
2, በአሥሩ መራሕያን መዘርዘራቸው

የመሆንና የመኖር ግሦች

Verb to be & verb to have

የመሆን ግሦች /Verb to be

- በአማርኛ የመሆን ግሦች የምንላቸው በቁጥር ምን ያህል ናቸው?
- በ8ቱ ተውላጠ ስሞች ልክ በያንዳንዱ 3ት 3ት የመሆን ግሦች አሉ (የሀላፊ፣ የአሁን፣ የትንቢት)፤ ስለዚህ በድምሩ 24 ናቸው ማለት ይቻላል።

ያው እንደምታዉቁት...

- ባለፈው ሰሞን በተደጋገመ አኳኋን በግእዝ ቋንቋ ውስጥ **10 መራሕያን** እንዳሉና እያንዳንዳቸውም ደግሞ የመሆን ግስ (ነባር አንቀጽ) በመሆን እንደሚያገለግሉ ተመልክተናል።

➢ሀሰቴን ነውን እንዴ በሉ ኣ ኢትዮጵያዊያን 🤷

ለማስታወስ ያክል

በግእዝ ግን ራሳቸው መራሕያን የመሆን ግሶች ናቸው።

- አነ=ነኝ፣ነበርኩ፣እሆናለው
- ንሕነ=ነን፣ነበርን፣እንሆናለን
- አንተ= ነህ፣ነበርህ፣ትሆናለህ
- አንቲ= ነሽ፣ነበርሽ፣ትሆኛለሽ
- **አንትሙ/ን**=ናችሁ፣ነበራችሁ፣ትሆናላችሁ
- ውእቱ=ነው፣ነበር፣ይሆናል
- ይእቲ = ናት፣ነበረች፣ትሆናለች
- **ውእቶሙ/ን**=ናቸው፣ነበሩ፣ይሆናሉ

ውእቱ

- ከአስሩ መራህያን ውስጥ ግን በተለየ መንገድ የምናየው "**ውእቱ**" ነው።
- ውእቱ ለአስሩም መራህያን የመሆን ግስ ይሆናል።
- **በዚህ ጊዜ ትርጉሙ እንደ አረፍተ ነገሩ ባለቤት ይወሰናል።**

ምሳሌወች

- አነ ውእቱ=እኔ ነኝ
- አንተ ውእቱ =አንተ ነህ
- አንቲ ውእቱ=አንች ነሽ
- መኑ ውእቱ=ማን ነው
- ባዩሽ ውእቱ=ባዩሽ ናት

😂😂😂

አኮ➔አይደለም

- **የውእቱ ተቃራኒ ነው።**
- ይኸም ለአስሩ መራህያን **<u>አፍራሽ/አሉታዊ የመሆን</u>** ግስ በመሆን ያገለግላል።
- ስለዚህ ትርጉሙ እንደ ባለቤቱ ይወሰናል።

ምሳሌያት

- አነ አኮ ሰራቂ =እኔ ሌባ አይደለውም
- አንቲ አኮ =አንቺ አይደለሽም
- ንህነ አኮ ከላባት=እኛ ውሾች አይደለንም
- አንተ አኮ አበድ=አንተ ሰነፍ አይደለህም
- አንትሙ አኮ ሐለስትዮ =እናንተ ጦጣ አይደላችሁም (ወ)
- አንትን አኮ ሐታቲያት =እናንተ መርማሪዎች አይደላችሁም (ሴ)
- ውእቱ አኮ መርድዕ=እሱ ተማሪ አይደለም
- ይእቲ አኮ ስንኳቲት=እሷ ቀዶ ጠጋኝ አይደለችም
- ውእቶሙ አኮ ሰበእ=እነርሱ ሰወች አይደሉም （ወ）
- ውእቶን አኮ ሔራት=እነርሱ ቸሮች አይደሉም (ሴ)

የመኖር ግሦች /verb to have

የ"በ" ትርጉም

- በቁም ቀሪ (በ) ምሳሌ፡- ኤልያስ ዐርገ በሰረገላ እሳት።
- ለ ተናፀሩ ገጽ በገጽ።
- በ _ጊዜ በምንዳቤየ ተዘከርኩከ።

ዘብ – ያለ። ዘበሰማያት – በሰማያት ያለ፤ ዘ – የ። «ያለ» ያስባለው «ብ» ነው።

ብብ – በእየ። በበ ዕለቱ – በየ ዕለቱ

ብ – በ፣ ን፣ ጋር፣ ችሎታ፣ ጊዜ፣ ለ፣ ወደ፣ እንደ፣ ስለ ይሆናል

1) ቦ--- አለ፤ ኖረ፤ ነበረ

ሀ, ቦ ጊዜ ለኵሉ።(የ "ቦ" ትርጉም አለው)

ለ , ቦ አዳም ውስተ ገነት መጠነ ሰብዐቱ ዓመት።(የ "ቦ" ትርጉም ነበረ)

ሐ, ቦ እለ ይብሉከ ዮሐንስሃ መጥምቅ።(የ "ቦ" ትርጉም አሉ)

የ “በ” ዘሮች ሁለት ጥቅሞች አሏቸው

1. መደበኛ ሆነው ሲያገለግሉ =የመኖር ግሥ

2.ተቀባይ ሆነው ሲያገለግሉ=ከግሥ ቀጥለው ይመጣሉ።

ትርጉማቸውንም ደግሞ ዝቅ ብለን እንወያይበታለን

- አነ➔ብየ
- ንሕነ➔ብነ
- አንተ➔ብከ
- አንቲ➔ብኪ
- አንትሙ➔ብክሙ

- አንትን➔ብክን
- ውእቱ➔ቦቱ/ቦ
- ይእቲ➔ባቲ/ባ
- ውእቶሙ➔ቦቶሙ/ቦሙ
- ውእቶን➔ቦቶን/ቦን

ሀ. መደበኛ ሆነው ሲያገለግሉ

- **ብየ➔** በእኔ፣አለኝ፣አለብኝ፣ኖረብኝ፣ነበረብኝ፣ነበርሁ፣አለሁ፣ ኑሮኛል፣ ኑሮብኛል፣ ኖረኝ፣ኑሮልኛል፣ ይኑርልኝ
- ብነ➔
- ብከ➔
- ብኪ➔
- ብክሙ➔
- ብክን➔
- ቦ/ቦቱ➔
- ባቲ/ባ➔
- ቦቶሙ/ቦሙ➔
- ቦቶን/ቦን➔

- ብኪ ልህቀት ሀገሪትነ
- ብክሙ መጻብነ ምንዳቤ
- ዘቦቱ ኩሉ ኮነ
- ብከ ተወጠነ ዝ ዐቢይ ግብር
- ወብነ ተፈጸመ
- ቦቱ እዳ
- ቦ ጊዜ ለኩሉ
- ይእቲ ባቲ አሐቲ እኅት
- **አነ ብየ ፈተና ጌሰም**
- ንሕነ ብነ ብዙኅ ግብር በዝ ሰሞን
- እላ ቦቶን ክልኤተ ህሙማን
- ብኪ ወጽዐ አዳም እምሲዖል
- ብከ ንመውዖሙ ለኵሎሙ ፀርነ

ለ. ተቀባይ ሆነው ሲያገለግሉ

- ብየ=ብኝ
- ብነ=ብን
- ብከ=ብህ
- ብኪ =ብሽ
- ብክሙ =ባችሁ
- ብክን=ባችሁ (ሴ)

- ቦቱ=በት
- ባቲ=ባት
- ቦቶሙ/ቦሙ=ባቸው
- ቦቶን/ቦን=ባቸው （ሴ)

- ውእቶን ወለዳብየ
- ዝህብ መጽአ ቦቱ
- ኅድግ እኍነ ኢትሑርብነ
- እማ ሖረት ባቲ
- ማእዜ ሖረብከ ዱድከ
- ዘቦ እዝን ሰሚዐ ለይስማዕ
- ዕዳ ቦሙ
- በጽሐ ቦቱ
- **ቦ ጊዜ ለኩሉ**
- **ብየ ሰይጣን ፀርየ**

ሐ. ራሱን ሳይለውጥ ከመራሕያን ጋር ይነገራል፤ ቦ-እንደ መገኘት/መኖር

- ቦ አነ➔ኑሪያለሁ፣ ኖርኩ፣ ነበርኩ
- ቦ ንሕነ➔
- ቦ አንተ ➔
- ቦ አንቲ➔
- ቦ አንትሙ➔
- ቦ አንትን➔
- ቦ ውእቱ➔
- ቦ ይእቲ➔
- ቦ ውእቶሙ➔
- ቦ ውእቶን➔

- ቦ አነ ባህቲትየ
- ቦ ንሕነ ውስተ ዓለም
- ዘ መኑ ቦ አንቲ

አለበ

❖ የ "በ" ዝርዝሮች አፍራሻቸው **አል-** ሲሆን የ "ለ" ዝርዝሮች ግን አፍራሽ የላቸውም።

አለበ--- የለም፣ አልኖረም፣ አልነበረም

- አልብየ=የለኝም
- አልብነ=የለንም
- አልብከ=የለህም
- አልብኪ=የለሽም
- አልብክሙ=የላችሁም

- አልብክን =የላችሁም
- አልቦቱ/አልቦ➔የለውም
- አልባቲ/አልባ➔የላትም
- አልቦቶሙ/አልቦሙ➔የላቸውም
- አልቦቶን/አልቦን➔የላቸውም

- **ምሳሌ ፡-**

ሀ, አልብነ ንጉሥ ዘእንበለ ቄሣር

ለ, አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ

ሐ, አልቦ ዘያድኅነከ እምእዴየ

መ, ዝንቱ ተመሀሪ አልቦቱ ድፍተር

ሠ, አልቦቱ ውእቱ ውስተ ቤተ ትምህርት

ረ, ዝኩ ነገርሰ አኮ ብየ አው ኢ መጽአ ብየ

የ “ለ” እርባታ

- “ለ” ደቂቅ አገባብ ሲሆን በነባር አንቀጽነቱ በመኖር ግሥነቱ ይፈታል።

የ”ለ” ትርጉም

- በቁም ቀሪ.........................(ለ) **ምሳሌ** ፦ ሰድ ሎቱ መጽሐፎ ለእኍከ፣ ስብሐት ለእግዚአብሔር
- ዘርፍ አያያዥ......................... (የ) ወረዱ ግብጸ ዉሉዱ ለያዕቆብ
- ተጠቃሽ ተሳቢ......................... (ን) ንሴብሖ ለአምላክነ፣ አክብርዋ ለቤተ ክርስቲያን፣ ይቤልዎ አይሁድ ለኢየሱስ
- አዳማቂ .... (ትርጉም የለሽ) ዘጸምዐ ለይምጻዕ ኀቤየ

በአጠቃላይ ለ ፡የ፣ን፣ዘ፣ተ፣ወደ፣ አዳማቂ፣ ተቀባይ፣አቀብሎ፣ ሽሺ፣ ላይ፣ በ፣ ስለ፣ መኾን ይችላል።

መደበኛ ሆነው ሲያገለግሉ

- ሊተ/ልየ➔ ለእኔ፣ እኔን፣ ለእኔ(*ተጠቃሽ ተውላጠ ስም*) አለኝ፣ አለልኝ፣ ኖረልኝ፣ ነበረልኝ፣ ይገባኛል፣ይኖረኝ ነበር፣ ይኖራኛል፣ ይኖረኝ ይኾናል፣ ነበረኝ
- ለነ➔
- ለከ➔
- ለኪ➔
- ለክሙ➔
- ለክን➔
- ሎቱ➔
- ላቲ➔
- ሎሙ/ሎቶሙ➔
- ሎን/ሎቶን➔

- ለከ ንፌኑ ልዑለ ውዳሴ
- ሎቱ ስብሐት
- ላቲ ስብሐት
- ለነ ለአግብርቲከ ሀበነ አዕይንተ አእምሮ
- ሰላም ለክሙ
- ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ማርያም እምነ ናስተበቍዐኪ
- ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወ ተበቀል በቀልየ
- ልበ ንጹሐ ፍጠር ሊተ
- ለሊሁ ፈጣሪነ ተሰቅለ ለነ

❖ ተቀባይ ሆነው ሲያገለግሉ

- ልየ/ሊተ=ልኝ
- ለነ=ልን
- ለከ=ልህ
- ለኪ=ልሽ
- ለክሙ=ላችው
- ለክን=ላችው（ሴ）
- ሎቱ=ለት
- ላቲ=ላት
- ሎቶሙ/ሎሙ=ላቸው
- ሎቶን/ሎን=ላቸው（ሴ)

- አሕየወት ሊተ
- ብልዐ ሊተ
- ፈነወ ላቲ
- ሰገደ ላቲ
- መጽአት ለከ
- አምጽኡ ላቲ አምሐ
- ሰዐሊ ሊተ
- ሰአሊ ልየ
- ይብልዐኒ ሎቱ፡ ይብላኝለት
- ንዒ ለከ፡ × አይባልም አ

፬, ግዑዝ ግሥ፡- ይህ የግሥ ዓይነት ደግሞ በቅርጸ ቀለማቱ ገቢር ግሥን ሲመስል ቃላትን ባለመሳቡ ተገብሮ ግሦችን ይመስላል።ስለሆነም ይህንን የግሥ አይነት "**ተ**"ን በመጨመር ወደ ተገብሮ ግሥ መቀየር አይቻልም።

- ይህም የሆነው በራሱ የተገብሮ ግሥ ፀባይ ስላለው ነው። ብዙ መጻሕፍት ግዑዝ ግሥን በተገብሮ ግሦች ውስጥ ያካትቱታል።
- ምሳሌ፡- ኖመ--- አንቀላፋ፣ተኛ
- ሞተ--- ሞተ
- ቆመ--- ቆመ
- ፆመ--- ፆመ
- ሖረ--- ሄደ
- ደግደገ--- ከሳ
- ሰከበ--- ተኛ
- ኀየ--- ሸሸ ወዘተ...

መራኁት(የግሥ መነሻዎች)

- ***መርኆ***= *መክፈቻ* የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ***መራኁት***=*መክፈቻዎች* ነው።“
- *አርኀወ = ከፈተ*“ ካለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን መራኁት የሚባሉት የግሥ መነሻ ፊደላት ናቸው።
- በግእዝ ሰዋስው ግሦች የሚነሱት በአምስት ፊደላት ብቻ ነው፡- እነርሱም (**ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ** እና **ሳብዕ** ናቸው፤ በ***ካዕብ*** በ***ሣልስ*** አይጀምርም።

- **ማስታወሻ፡**

1. ግሦች ሁሉ መነሻቸው ይለያይ እንጅ መድረሻቸው ሁልጊዜ **ግእዝ** ቀለም ነው። ግን ከ "**ይቤ**" ውጭ ነው ።**ይቤ**ማ እንድ ነባር አንቀጽ አይደለምን ቢሉ "ካልዓዩን፣ ዘንዱን ፣ ት እዛዙን ") ይዞ በመገኘቱ ነው።
2. ነጠላ ግስ ከ ሁሉት ፊደል አይወርድም፡ ከ አራት አይወጣም፡ ለማድና ባዕድ ሲጨመር ግን 5ትም ፡ 6ትም 7ትም ይሆናል፤ ቢበዛ ከ**ሰባት** አይበልጥም።

ምሳሌ፡-

- ዔለ፣ ሤጠ፣......................**ሁለት** ሆህያት
- አስተስነአለ➔**አሰነባበተ** (ባለሰባት ሆህያት) /ረጅሙ ግስ/

- የግእዝ ቋንቋ አጠናን ዘዴ እንደየ ቅኔ ቤቱ ስርዓት የተለያየ ቢሆንም እንኳን ከሁሉ በፊት የግእዝ ቃላት በመሸምደድ፤ እሚረቡ ከሆኑ ደግሞ **አወራረዳቸውን** ጨምሮ በ**ዝርዝር** ይጠናሉ።

- በዚህ መንገድ ግሶቹ ከ **ሀ - ፐ** ያሉት ቃላት እየተጠኑ እና እየተዘወተሩ ሲሄዱ ትርጉማቸው ከነ ሰዋስው ሙያቸው ይለመዳሉ።
- ለዚህም አይነት አወራረድ ደግሞ ነባር አለው፤ ይህን አይነት ያለውን ቅደም ተከተል እና ዝርዝር ከለየ በኋላ ተማሪው ቃላትን በማያያዝ አ.ነገር መስራት ይጀምራል፤ምክንያቱን ቃላትን ብቻ መሸምደድ ጠቃሚው ስላይደለ የያዛቸውን ቃላት በአጭር አ.ነገር እንዲያውላቸው ይገደዳል።
- ምሳሌ፡- በልአ ኅብስተ _ እንጀራን በላ።

❖**ይህንንም ሲያደርግ የሰዋስው ጸያፎችን ሊጠነቀቃቸው ይገባል።**

የግሥ አረባብ ስልት

- በመጀመሪያ ግሶችን በእርባታ ጊዜ ካላቸው ሚና አንጻር በሦስት ይከፈላሉ፡፡
  1. አርእስት➔አለቆች
  2. ሰርዌ(ሰራዊት)➔አባል ፣መሪውን የሚመስል
  3. ስረይ➔መሪም ተመሪም ያልሆነ(አመለኛ ግሶች)

፩) <u>አርእስተ ግሥ</u>

- በልሳነ ግእዝ ውስጥ “**ርእስ**” የሚለው ቃል ራስ/አለቃ/መሪ ለማለት ያክል ሲሆን “**<u>አርእስት</u>”** የሚለው ሲበዛ ደግሞ “***<u>ራሶች/አለቆች/መሪዎች</u>***” ይሆንልናል ስለዚህ አርእስተ ግሥ ማለት የግሥ አለቆች የሚል ፍች ይሰጠናል።
- በአጠቃላይ በአብዛኞች መጻሕፍት መሠረት ***መሪ ግሦች***ን በስምንት (8) ይከፍሏቸዋል።

- አርእስተ ግሶች （መሪወች） እንዴት እንደሚረቡ ላወቀ ሰው ተመሪዎቹ （ሰራዊት） እንዴት እንደሚረቡ ማወቅ አያቅተውም ።
- የያንዳንዱን አርእስተ ግሥ ባህሪ ጠንቅቆ በማወቅ አዲስ ግስ ሲያጋጥም ይህ የእከሌ ሰርዌ ነው በማለት በዚያ ህግ መሰረት ማርባት ይቻላል።

❖ **ምንም እንኳን ብዙ ሕገወጥ እርባታዎች ቢገኙም ደንበኞቹ ግሶች ግን አርእስተ ግሶችን ይከተላሉ።**

አርእስተ ግሦችን የመለያ መስፈርቶች

1) ሆሄያት ብዛት
2) የሆሄያት ቅርጽ
3) አነባበብ（ጠብቆ/ሳልቶ）

የቀጠለ...

- ከስምንቱ አርእስተ ግሦች አራቱ በግእዝ ፊደል ይጀምራሉ
  - **ቀተለ፣ ቀደሰ፣ ገብረ፣ ተንበለ**
- በራብዕ （ባረከ）
- በኃምስ （ዴገነ）
- በሳድስ （**ክህለ**）
- በሳብዕ （**ጦመረ**）

ስምንቱ አርእስተ ግሥ

ሀ, ቀተለ =ገደለ

✓ሦስት ሆሄያት ብቻ አሉት

✓ሦስቱም ሆሄያት ግእዝ ብቻ የሆኑ በግእዝ የተነሳ

✓ላልቶ ይነበባል

❖**ማስታወሻ፡-**ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪም የቀተለ ሰራዊት የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

1. ሁለት ቀለም የኾኑ በግእዝ ተነስው በግእዝ የጨረሱ ይኸውም የጠበቀ “**ሐመ**”ን፣ “**ነደ**”ን ፣ “**ጠለ**”ን ፣ “**ቀለ**”ን፣ “**ጠበ**”ን የመሳሰለ ግሶች
2. ሁለት ቀለም ኾነው፣ በኃምስ የተነሱ፣ ላልተው የሚነበቡ፣ በግእዝ የሚፈጽሙ ግሶች ይኸውም “**ሤመ**”ን፣ “**ቴሀ**”ን፣ “ዔለ”ን፣ “**ሄደ**”ን፣ “**ኬደ**”ን የመሳሰለ ግሶች
3. ሁለት ቀለም ኾነው፣ በሳብዕ ተነስተው፣ ላልተው የሚነበቡ፣ በግእዝ የሚፈጽሙ ግሶች ይኸውም “ሖረ”ን፣ “ዖደ”ን፣ “ጾመ”ን፣ “ቆመ”ን የመሳሰሉ ግሶች

<u>ሰ, ቀደሰ ➔ አመሰገነ</u>

- ✓ሦስትና ከዚያ በላይ ሆሄያት ያሉት
- ✓በግእዝ የተነሳ / መካከሉ ግእዝም ሳድስም ይሆናል
- ✓<u>ጠብቆ የሚነበብ</u>

ሐ, ገብረ ➔ ሰራ/አደረገ

- ✓ሦስት ሆሄያት ብቻ ያሉት
- ✓መካከሉ ሳድስ የሆነ በግእዝ የሚነሳ
- ✓ሳልቶ የሚነበብ

<u>መ, ተንበለ➔ ለመነ</u>

- ✓አራትና ከአራት በላይ ሆህያት ያሉት
- ✓መነሻው ግእዝ መካከሉ ሳድስና ግእዝ የሆነ
- ✓ሳልቶ የሚነበብ

ሠ, ባረከ➔ አመሰገነ/መረቀ/ባረከ

- ✓ሦስትና ከዚያ በላይ ሆህያት ያሉት
- ✓በራብዕ የተነሳ / መካከሉ ግእዝ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል
- ✓ላልቶ የሚነበብ

ረ, ዴገነ➔ተከተለ ወይም (ሴሰየ)➔መገበ

- ✓ሦስትና ከዚያ በላይ ሆሄያት ያሉት
- ✓በኃምስ የተነሳ / መካከሉ ግእዝ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል
- ✓ላልቶ የሚነበብ

ሰ, ክህሉ➔ቻሉ

✓ሦስት ሆሄያት ብቻ ያሉት

✓መነሻው ሳድስ የሆነ / ድኅረ መነሻው ሁልጊዜም ሰድስ ነው

✓ሳልቶ የሚነበብ

ቀ, ጠመረ=ጻፈ

- ✓ ሦስትና ከዚያ በላይ ሆሄያት ያሉት
- ✓ በሳብዕ የተነሳ
- ✓ ሳልቶ የሚነበብ

፪. ሰርዌ(ሰራዊት)

- ከላይ በተመለከትናቸው የአርእስተ ግሥ መለያዎች መሠረት ሌሎች ግሦች ከአርእስት ግሥ አንዱን ይከተላሉ።

የቀተለ ቤተሰቦች

1 ሐተተ =መረመረ

2 መሀለ =ማለ

3 ወሀበ =ሰጠ

4 ነቀወ =ጮኸ

5 ከወወ =ቀለጠፈ

6 ወረደ =ወረደ ....**ወዘተርፈ**

የቀደሰ ቤተሰቦች

1 ሰብሐ= አመሰገነ

2 ሰበወ =ልብ አደረገ

3 ተሰፈወ =ተስፋ አደረገ

4 ተወከለ =ታመነ

5 ተነበየ =ትንቢት ተናገረ

6 ሀለወ =ኖረ

7 ኀለየ =አሰበ

8 ተመክሐ =ተመካ

9 አንገለገ=አከማቸ... **ወዘተርፈ**

የገብረ ቤተሰቦች

1 ሰክረ =ሰከረ

2 መልሐ= መዘዘ

3 ወድቀ =ወደቀ

4 መስወ =ቀለጠ

5 መስየ =መሸ .... **ወዘተርፈ**

የተንበለ ቤተሰቦች

- አድለወ =አደላ
- አጥረየ= ገዛ፡ ገንዘብ አደረገ
- አመንተወ =መንታ አደረገ
- አመከንየ =አመካኘ
- አመድበለ= ሰበሰበ ፡ አከማቸ
- አንቀልቀለ =አናወጠ
- አንሰሐሰሐ= አንቀሳቀሰ
- አቅየሐይሐ =አቅላላ
- አስተሰነአለ =አሰናበተ
- ቀበያውበጠ= ቀላወጠ....................................... **ወዘተርፈ**

የባረከ ቤተሰቦች ...

1 ሣረረ =ሰራ

2 ፃመወ =ደከመ

3 ሣቀየ= አናወጠ

4 ፃዕደወ =ነፃ

5 ፃህየየ= አረመ

6 ማኅረከ= ማረከ........................ **ወዘተርፈ**

የዴገነ ቤተሰቦች …

1 ቆቅሀ =ፈተገ

2 ዜነወ= ነገረ

3 ጌገየ =በደለ

4 ዔወወ =ማረከ

5 ሴሰየ=መገበ……………… **ወዘተርፈ**

የክህሉ...

1 ውኀዘ =ፈሰሰ

2 ስሕወ =ሳበ / ጎተተ

3 ጥዕየ =ዳነ

4 ጥዕመ=ቀመሰ

5 ንእደ=አማረ............... **ወዘተርፈ**

የጠመረ…

1 ኖሠሠ= ጠረገ

2 ቶስሐ =ጨመረ

3 ሞርቅሐ =ላጠ

4 ሎለወ =ጠበሰ……………… **ወዘተርፈ**

የግሥ አረባብ (አንቀጽ/ረባሐ ግስ/ tenses

✓**አንቀጽ** ማለት ግሥ እና ዘሮቹ በአረፍተ ነገር ውስጥ ማለት ነው።

✓ሁለት አይነት አናቅጽ አሉ፤ አከፋፈላቸውም የማሰር አቅማቸውን መሰረት አድርጎ ነው።

- ማሰሪያ አንቀጽ መሆን ከቻለ

  ➔**ዐቢይ አንቀጽ**

- ማሰሪያ አንቀጽ መሆን ካልቻለ

  ➔**ንዑስ አንቀጽ**

- ግሶችን በምናረባት ጊዜ በሁለት መንገድ ተከትለን ማየት እንችላለን።

ይኸውም፦

1. ንዑስ (መለስተኛ/የዋህ) እርባታ
2. ዝርዝር(ውስብስብ/መሰሪ) እርባታ

፩. ንዑስ (መለስተኛ/የዋህ) እርባታ

✓ ይኸ የእርባታ ዘዴ አንድን ግስ በሚከተሉት ዘዴዎች በአሰሩም መራህያን በምንችለው መንገድ የምናስኬደውን ትንተና መሠረት ያደረገ ነው።(ኹሉንም በየተራ የምናያቸው ይኾናል)

፩. ኀላፊ ቀዳማይ አንቀጽ(past
፪. ካልዓይ አሁን እና መጻኢ (present &future)
፫. በዘንድ እና በትእዛዝ
፬. ንዑስ አንቀጽ-Infinitive

አንቀጽ (ዐቢይ ፤ ንዑስ)

ሀ. ዐቢይ ኣንቀጽ

1. ኀላፊ /ቀዳማይ ኣንቀጽ(past tense)/**perfective/**
2. ትንቢት /ካልዓይ ኣንቀጽ (present &future continous) /**Imperfective/**
3. ትእዛዝ /ራብዓይ ኣንቀጽ(command/*Subjective***)**

A. ቀዳማይ አንቀጽ

የግሥ እርባታ በአሥሩ መራሕያን፡- ከሶስተኛ መደብ ዉጭ ላሉት መራሕያን የግሱን የመጨረሻ ፊደል ወደ **ሳድስ** በመጀመሪያ ከለወጥን በኋላ ከዚህ ቀጥለው የተመለከቱትን ቅጥያዎችን በመጨመር እንዘረዝራለን።

- አነ ➔ ኩ=ኩ
- ንሕነ➔ነ=ን
- አንተ➔ከ=ህ
- አንቲ➔ኪ=ሽ
- አንትሙ➔ክሙ=አችሁ
- አንትን ➔ክን=አችሁ (ሴ)
- ውእቱ____
- ይእቲ➔ት=ች
- ውእቶሙ➔ኡ= ሉ
- ውእቶን➔ኣ=ሉ (ሴ)

ቀተለ

- አነ ቀተልኩ=ገደልኩ
- ንሕነ ቀተልነ=ገደልን
- አንተ ቀተለከ=ገደልህ
- አንቲ ቀተልኪ=ገደልሽ
- አንትሙቀተልክሙ=ገደላችሁ
- አንትን ቀተልክን=አናንተ ገደላችሁ（ሴ）

- ውእቱ ቀተለ=እሱ ገደለ
- ይእቲ ቀተለት=እሷ ገደለች
- ወእቶሙ ቀተሉ=እነርሱ ገደሉ
- ውእቶን ቀተላ=እነርሱ ገደሉ（ሴ）

ቀደሰ

- ቀደስኩ
- ቀደስነ
- ቀደስከ
- ቀደሰኪ
- ቀደስኪ
- ቀደስክሙ
- ቀደስክን

- ቀደሰ
- ቀደሰት
- ቀደሱ
- ቀደሳ

የ “ገብረ” ቤቶች ምሳሌ

ሰምረ➔ ወደደ

- አነ ሰመርኩ
- ንሕነ ሰመርነ
- አንተ ሰመርከ
- አንቲ ሰመርኪ
- አንትሙ ሰመርክሙ
- አንትን ሰመርክን

- ውእቱ ሰምረ
- ይእቲ ሰምረት
- ውእቶሙ ሰምሩ
- ውእቶን ሰምራ

ተንበለ

- ተንበልኩ
- ተንበልነ
- ተንበልከ
- ተንበልኪ
- ተንበልክሙ
- ተንበልክን

- ተንበለ
- ተንበለት
- ተንበሉ
- ተንበላ

ባረከ

- ባረኩ
- ባረክነ
- ባረክ
- ባረኪ
- ባረክሙ
- ባረክን
- ባረከ
- ባረከት
- ባረኩ
- ባረካ

ዴገነ

- ዴገንኩ
- ዴገነ
- ዴገንከ
- ዴገንኪ
- ዴገንከሙ
- ዴገንክን
- ዴገነ
- ዴገነት
- ዴገኑ
- ዴገና

ክህለ

- ክህልኩ
- ክህልነ
- ክህልከ
- ክህልኪ
- ክህልክሙ
- ክህልክን

- ክህለ
- ክህለት
- ክህሉ
- ክህላ

ጠመረ

- ጠመርኩ
- ጠመርነ
- ጠመርከ
- ጠመርኪ
- ጠመርክሙ
- ጠመርክን

- ጠመረ
- ጠመረት
- ጠመሩ
- ጠመራ

አመለኛ ግሶች በቀዳማይ አንቀጽ

1. በ"ሀ" እና በ"አ" የሚጨርሱ ግሶ ች ሲዘረዘሩ በአንደኛ እና በሁለተኛ መደብ ቅድመ መድረሻቸውን ወደ ራብዕ ይለውጣሉ፡፡

በ"ሀ" እና በ"አ" የሚጨርሱ ግሶ ች ሲዘረዘሩ

- አነ በላዕኩ=እኔ በላሁ
- ንሕነ በላዕነ
- አንተ በላዕከ
- አንቲ በላዕኪ
- አንትሙ በላዕክሙ
- አንትን በላዕክን
- ውእቱ በልዐ
- ይእቲ በልዐት
- ውእቶሙ በልዑ
- ውእቶን በልዓ

የቀጠለ…

- ረባሕኩ
- ረባሕነ
- ረባሕከ
- ረባሕኪ
- ረባሕክሙ
- ረባሕክን
- ረብሐ
- ረብሐት
- ረብሑ
- ረብሓ

N.B የ"ሀ" እና የ"አ" አመል ሁለት ቀለማት ብቻ ባላቸው ግሶች አይታይም

- ሦዕኩ
- ሦዕነ
- ሦዕከ
- ሦዕኪ
- ሦዕክሙ
- ሦዕክን
- ሦዐ
- ሦዐት
- ሦዑ
- ሦዓ

2. “**ቀ፣ ከ፣ ገ**” በግስ መድረሻ ላይ ሲገኙ በሁለተኛ መደቦች & በአንደኛ መደብ ”በ**እኔ**” ጊዜ አመልካቹን የ “**ከ**” ን ዘር ማስገባት ትተው ጠብቀው ይነበባሉ፡፡

በ"ቀ"

- አነ ወረቑ
- ንሕነ ወረቅነ
- አንተ ወረቀ
- አንቲ ወረቂ
- አንትሙ ወረቅሙ
- አንትን ወረቅን
- ውእቱ ወረቀ
- ይእቲ ወረቀት
- ውእቶሙ ወረቁ
- ውእቶን ወረቃ

በ“ገ”

- አነ ኀደጕ
- ኀደግነ
- አንተ ኀደገ
- ኀደጊ
- አንትሙ => ኀደግሙ
- አንትን => ኀደግን
- ውእቱ ኀደገ
- ኀደገት
- ውእቶሙ ኀደጉ
- ኀደጋ

በ“ከ”

- አነ ➔ ሰበኩ
- ንሕነ➔ሰበክነ
- አንተ ➔ሰበ<u>ከ</u>
- አንቲ➔ ሰበ<u>ኪ</u>
- አንትሙ➔ ሰበ<u>ክሙ</u>
- አንትን➔ሰበ<u>ክን</u>
- ውእቱ ➔ሰበከ
- ይእቲ➔ሰበከት
- ውእቶሙ➔ሰበኩ
- ውእቶን ➔ ሰበካ

3. “ነ” በግስ መድረሻ ላይ ሲገኝ በንሕነ ጊዜ ብቻ ባልንጀራውን “ነ”ን ውጦ ጠብቆ ይነበባል፡፡

- ማሰንኩ
- ንሕነ➔ማሰ**ነ**
- ማሰንከ
- ማሰንኪ
- ማሰንክሙ
- ማሰንክን
- ማሰነ
- ማሰነት
- ማሰኑ
- ማሰና

4. በክህለ ቤቶች “የ” በስተመጨረሻ ሲገኝ

- በሁለተኛ እና በአንደኛ መደብ ቅድመ መድረሻውን ሳልስ አድርጎ ራሱን ይጎርድና የተለመዱትን ቅጥያዎችን መጨመር ነው።

ምሳሌ

- ርኢኩ
- ርኢነ
- ርኢከ
- ርኢኪ
- ርኢክሙ
- ርኢክን
- ርዕየ
- ርዕየት
- ርዕዩ
- ርዕያ

5. በገብረ ቤቶች ዝርዝር በሁለተኛ እና በአንደኛ መደብ የመካከለኛውን ሳድስ ቀለም ወደ ግእዝ ቀለም ተለውጦ ይዘረዘራል፡፡

- **ገብረ**➔ ገበርኩ፣ገበርነ፣ገበርከ፣ገበርኪ፣ገበርክሙ፣ገበርክን፣ገብረ፣ገብረት፣ገብሩ፣ገብራ
- **ሠምረ**➔
- **ለብሰ**➔

B. ካልዓይ፣ ሣልሳይ እና ራብዓይ አናቅጽ

- ዘንድ አንቀጽ/ሣልሳይ አንቀጽ (Jussive(In order to) _የዐቢይ አንቀጽ መደብ ሳይሆን የንዑስ አንቀጽ ክፍል ነው፤ ነገር ግን በግስ እርባታ ጊዜ ትእዛዝ አንቀጹን ስለሚመስል አብረን ለማየት እንዲመቸን ስንል በዐቢይ አንቀጽ ስር እንመለከተዋለን።

አስራው ፈደላት

- ስር➔መሠረት አስራው➔ስሮች

- አስራው ፈደላት/ቀለማት ማለት **ትንቢት፣ ዘንድ፣ ትእዛዝ** አንቀጾችን ከቀዳማይ አንቀጻቸው ላይ በመነሳት በአስሩ መራሕያን ለማርባት የሚጠቅሙ ቀለማት ናቸው።
- *በትንቢት፣ በዘንድ እና በትእዛዝ አናቅጽ ላይ በመነሻ ላይ የሚገቡ ባዕዳን* ቀለማት (ቅጥያዎች/prefixes) ናቸው።
- → **“ይቤ”**ን በአንቀፅ እና በመራህያን ለማርባትም ይረዳሉ።

4 ናቸው በግእዝ፣በራብዕ፣በሳድስ ይገኛሉ

- ተ፣ ታ ፣ ት
- ነ ፣ ና ፣ ን
- አ ፣ ኣ ፣ እ
- የ ፣ ያ ፣ ይ

በአስሩ መራህያን ላይ የእስራው ቀለማት አገልግሎት

- አነ➔ አ ፣ ኣ ፣ እ
- ንሕነ➔ ነ ፣ ና ፣ ን

- ውእቱ
- ውእቶሙ
- ውእቶን

→ የ ፣ ያ ፣ ይ

- አንተ
- አንቲ
- አንትሙ
- አንትን

→ ተ፣ታ ፣ ት

- ይእቲ➔ ተ፣ታ ፣ ት

ı. አስራው   በሳድስ ሲገኙ

- ይህ የሚሆነው አመል በሌለባቸው ግሦች ና በ ይቤ ነው።

ኣነ

- ቀተልኩ=ገደልኩ
- **እ**ቀትል=እገድላለው
- **እ**ቅትል=እገድል ዘንድ
- **እ**ቅትል=ልግደል

ንሕና

- ቀተልና=ገደልን
- **ን**ቀትል=እንገድላለን
- **ን**ቅትል=እንገድል ዘንድ
- **ን**ቅትል=እንግደል

አንተ

- ቀተልከ=ገደልክ
- **ት**ቀትል=ትገድላለህ
- **ት**ቅትል=ትገድል ዘንድ
- ቅትል=ግደል

አንቲ

- ቀተልኪ=ገደልሽ
- **ት**ቀትሊ=ትገድያለሽ
- **ት**ቅትሊ=ትገድሊ ዘንድ
- ቅትሊ=ግደይ

አንትሙ

- ቀተልክሙ=ገደላችው
- ትቀትሉ =ትገድላላችሁ
- ትቅትሉ=ትገድሉ ዘንድ
- ቅትሉ=ግደሉ

አንትን

- ቀተልክን=ገደላችው
- ትቀትላ =ትገድላላችሁ
- ትቅትላ =ትገድሉ ዘንድ
- ቅትላ=ግደሉ

ውእቱ

- ቀተለ=ገደለ
- **ይ**ቀትል=ይገደላል
- **ይ**ቅትል=ይገድል ዘንድ
- **ይ**ቅትል=ይግደል

ይእቲ

- ቀተለት=ገደለች
- **ት**ቀትል=ትገድላለች
- **ት**ቅትል=ትገድል ዘንድ
- **ት**ቅትል=ትግደል

ውእቶሙ

- ቀተሉ=ገደሉ
- **ይ**ቀትሉ=ይገድላሉ
- **ይ**ቕትሉ=ይገድሉ ዘንድ
- **ይ**ቕትሉ=ይግደሉ

ውእቶን

- ቀተላ=ገደሉ
- **ይ**ቀትላ=ይገድላሉ
- **ይ**ቕትላ=ይገድሉ ዘንድ
- **ይ**ቕትላ=ይግደሉ

እስራው በራብዕና በግዕዝ ሲገኙ

አነ	ንሕነ
• አእመርኩ	• አእመርነ
• አአምር	• ነአምር
• ኣእምር	• ናእምር
• ኣእምር	• ናእምር

አንተ	አንቲ
• አእመርከ	• አእመርኪ
• ተአምር	• ተአምሪ
• ታእምር	• ታእምሪ
• አእምር	• አእምሪ

ኣንትሙ

- <u>ኣ</u>እመርክሙ
- <u>ተ</u>ኣምሩ
- <u>ታ</u>እምሩ
- <u>ኣ</u>እምሩ

ኣንትን

- <u>ኣ</u>እመርክን
- <u>ተ</u>ኣምራ
- <u>ታ</u>እምር
- <u>ኣ</u>እምር

ውእቱ

- አእመረ
- የአምር
- ያእምር
- ያእምር

ይእቲ

- አእመረት
- ተአምር
- ታእምር
- ታእምር

ውእቶሙ

- አእመሩ
- የአምሩ
- ያእምሩ
- ያእምሩ

ውእቶን

- አእመራ
- የአምራ
- ያእምራ
- ያእምራ

የይቤ እርባታ በ10ሩ መራህያን

- አነ **እ**ቤ
- ንሕነ **ን**ቤ
- አንተ **ት**ቤ
- አንቲ **ት**ቤሊ
- አንትሙ **ት**ቤሉ
- አንትን **ት**ቤላ
- ውእቱ **ይ**ቤ
- ይእቲ **ት**ቤ
- ውእቶሙ **ይ**ቤሉ
- ውእቶን **ይ**ቤላ

ምሳሌ

- ይቤ እግዚአብሔር በኦሪት አክብር አባከ ወእምከ
- ይቤ ክርስቶስ ተፋቀሩ በበይናቲክሙ
- ትቤ ማርያም ኀድግ ሎሙ ኀጢአቶሙ
- አንቲ ትቤሊ ዘአንበበ ተአምርየ ይድኀን
- ትቤ ብእሲተ አግዚኡ ነዐ ስክብ ምስሌየ
- አንተ ትቤ እወ እወ ወአነ እቤ አኮ አኮ
- ንሕነ ንቤ ንሕነ ኃያላን ወአጽራሪነ ይቤሉ አኮ ኃያላን አንትሙ
- አንትንሰ በኩለሄ ትቤላ ንሕነ ሠናያት ንሕነ ዳእሙ አንሰ ኢእብል
- አንትሙ ትቤሉ ውሉደ አብርሐም ንሕነ ወግብርክሙሰ እምእኩይ ውእቱ
- ይብል አብድ በልቡ አልቦ እግዚአብሔር

የ ይቤ ርባታ ለውእቱ በአራቱ አናቅጽ

- ይቤ
- ይብል
- ይበል
- ይበል

❖ ለሌሎቹ መራህያን ደግሞ የ"ውእቱ"ን መሰረት እያደረጉ ከፊት ለፊት እስራው ቀለማቸውን ማስቀደም ነው።

ካልዓይ

- ክርስቶስ ይመጽእ ዳግመ
- ዘይበልዕ ባሕቲቶ ይመውት ባህቲቶ
- ወትቀውም ንግስት በየማንከ

- **ሣልሳይ አንቀጽ** ሌላኛው ስሙ **ዘንድ አንቀጽ፣ እንድ(ዲ)፣ ል(ሊ**) አንቀጽ እየተባለም መጠራት ይችላል።

እቅትል➔እገድል ዘንድ፣እንድገድል፣ልገድል

ይቅትል➔ይገድል ዘንድ፣እንዲገድል፣ ሊገድል

- **ሰከለ**=አፈራ

እሰክል➔አፈራለሁ

አስክል➔አፈራ ዘንድ፣እንድአፈራ (እንዳፈራ)፣ ልአፈራ(ላፈራ)

ትእዛዝ

- ፈኑ እዴከ ወያድኅነነ
- ንዑ ኅቤየ
- ሑሩ እ
- ሑረ እምኔየ
- አድኅን ህዝበከ ወባርክ ርስተከ
- እገብር ዘዚአየ ወግበር ዘዚአከ

የ 8ቱ አርእስተ ግሦች ዐቢይ እርባታ

- የአምስቱ አርእስተ ግሦች ከሁለተኛ መደብ (ከአንተ፣አንቲ፣አንትሙ፣ አንትን) ውጭ ዘንድና ትእዛዝ አንቀጻቸው ተመሳሳይ ነው።
- እነዚህም 4ቱ በግእዝ የሚጀምሩት(**ቀተለ፣ ቀደሰ፣ ገብረ፣ ተንበለ**) እና **ክህለ** ናቸው።
- የቀሩት 3 አርዕስተ ግሦች ስናይ ግን ሦስቱም አንቀጻቸው ተመሳሳይ ይሆናል፤ እነዚህም ግሦች ባረከ ዴገነ ጦመረ
- ነገር ግን ትንቢቱ ላይ ቅድመ መድረሻ ፊደሉ ጠብቆ ይነበባል።

ቀተለ

- ይቀትል፡ይግደላል
- ይቅትል፡ይገድል ዘንድ
- ይቅትል፡ይግደል

- አቡየ ይቀትል ከይሴ=አባቴ እባብን ይገድላል
- ውእቱ ብእሲ ይቅትል ለሰብ ወጽአ =ያ ሰውየ ሰውን ይገድል ዘንድ ወጣ
- ይቅትል እሁከ አሀዱ ዝህብ =ወንድምህ አንድ ጅብ ይግደል

ቀደሰ

- ይቄድስ =ያመሰግናል
- ይቀድስ=ያመሰግን ዘንድ
- ይቀድስ=ያመስግን

ምሳሌ፡-

- ለምንት ውእቱ ሰብ ዘኢይቄድስ ለአምላኩ ኩለሄ=> ሰው አምላኩን የማያመሰግነው ለምን ነው
- ይቀድስ አምነ => ያመሰግን ዘንድ አመነ
- አነ እቤ ይቀድስ ለአምላኩ=> እኔ አምላኩን ያመስግን አልኩ

ገብረ

- ይገብር=ያደርጋል
- ይግበር=ያደርግ ዘንድ
- ይግበር=ያድርግ

❑ምሳሌ፡-

✓ሰብእሰ ይገብር ግብረ አርዌ=> ሰው ግን የአውሬን ስራ ይሰራል

✓ይግበር ተሠሜመ ባህቱ ኢርኢነ ዘገብሮ አላ ዘአጠፋሁ=> ይሰራ ዘንድ ተሾመ ግን የሰራውን አላየንም ያጠፋውን እንጂ

✓ይግበርለነ በከመ ተመነይነ=> እንደተመኘነው ያድርግልን

ተንበለ

- ይተነብል=ይለምናል
- ይተንብል=ይለምን ዘንድ
- ይተንብል=ይለመን

❑ **ምሳሌ፡-**

- ይተንብል ንተንብሎ => ይለምን ዘንድ እንለምነው
- ይተንብል ይርከብ=> እንዲያገኝ ይለምን

ክህለ

- ይክህል/ይክል=ይችላል
- ይከሀል=ይችል ዘንድ
- ይክሀል=ይቻል

❑ <u>**ምሳሌ፡-**</u>

- ይክህል ተውኔት=> ጨዋታ ይችላል
- ይከሀል ርዕየ=> ይችል ዘንድ አየ

ባረከ

- **ይባርክ=ይመርቃል**
- ይባርክ= ይመርቅ ዘንድ
- ይባርክ=ይመርቅ

ዴገነ

- ይዴግን=ይከተሳል
- ይዴግን=ይከተል ዘንድ
- ይዴግን= ይከተል

ጠመረ

- ይጠምር=ይጽፋል
- ይጠምር=ይጽፍ ዘንድ
- ይጠምር=ይጻፍ

ሰ. ንዑስ አንቀጽ

- አንቀጽን የተለያዩ መጽሀፍት በተለያየ ሁኔታ ሲከፍሉት እናነባለን....

1. **ውስጠ ዘ**
2. **አርዕስት**
3. **ቦዝ**
4. **ዘንድ አንቀጽ**

1. ውስጠ ዘ

- ውስጠዘ ማለት **ድብቅ ዘ** ፤ **የማይታይ "ዘ "** ማለት ነው፤ ዘ ደግሞ በዚህ አውድ "**የ**" ማለት ነው።
- ስለዚህ ውስጠዘ ማለት የማይታይ **"የ"** ማለት መሆኑ ነው፣፣
- በዚሁ ለማየትና ለማገናዘብ እንዲረዳ ግልጽ "የ" የሚባሉትን እንደ
  - እንተ →የ፣ለነጠላ ቁጥር
  - እለ→የ፣ለብዙ ቁጥር
  - ዘ→የ፣ለሁለቱም

የቀጠለ…

- ውስጠዘ ሁለት አይነት አለ
  - **ሣልስ ውስጠዘ**
  - **ሳድስ ውስጠዘ**

1.1 ሣልስ ውስጠዘ

- ግሱ የቅርጽ ለውጥ ካመጣ በኋላ የመጨረሻዋ ፊደል ሦስተኛ/ሣልስ/ስለምትሆን ነው
- ትርጉሙም እንደ ግሡ የሚወሰን ሆኖ ባጠቃላይ ግን “እንዲህ የአደረገ የሚል ይሆናል”።
- ምሳሌ የገደለ፣የአመሰገነ፣የተከተለ…

ከዚህ ቀጥለን የስምንቱን አርስተ ግሦች ሣልስ ውስጠ ዘ እንመለከታለን

ቀተለ➔ገደለ

- ቀታሊ=የገደለ፣የሚገድል፣ገዳይ፣(መ/ር ኢያሱ?)
- ቀታሊያን=የገደሉ ፣የሚገድሉ፣ገዳዮች （ወ)
- ቀታሊት=የገደለች፣የምትገድል፣ገዳይ
- ቀታሊያት=የገደሉ ፣የሚገድሉ፣ገዳዮች （ሴ)

ሣልስ ውስጠዘ በዐሥሩ መራሕያን ሲዘረዘር

- ቀታሊየ=የሚገድለኝ ገዳየ
- ቀታሊነ=የሚገድለን ገዳያችን
- ቀታሊከ =የሚገድልህ ገዳይህ
- ቀታሊኪ =የሚገድልሽ ገዳይሽ
- ቀታሊክሙ =የሚገድላችው ገዳያችው/ወ
- ቀታሊክን =የሚገድላችው ገዳያችው/ሴ
- ቀታሊሁ =የሚገድለው ገዳዩ
- ቀታሊሃ =የሚገድላት ገዳይዋ
- ቀታሊሆሙ =የሚገድላቸው ገዳያቸው/ወ
- ቀታሊሆን=የሚገድላቸው ገዳያቸው/ወ

ቀደሰ=አመሰገነ

- ቀዳሲ=የአመሰገነ፣የሚያመሰግን፣አመስጋኝ
- ቀዳስያን=የአመሰገኑ፣ የሚያመሰግኑ፣አመስጋኞች （ወ）
- ቀዳሲት= የአመሰገነች፣የምታመሰግን፣አመስጋኝ
- ቀዳስያት= የአመሰገኑ፣የሚያመሰግኑ፣ አመስጋኞች （ሴ）

- አንቲ ሰንጓቲት ኢትሁሪብየ

ለእመ ኢርዒኩኪ ይጠፍዕ ልብየ።

ገብረ =አደረገ/ሰራ

- ገባሪ=የሚያደርግ፣የአደረገ፣አድራጊ
- ገባርያን= የሚያደርጉ፣የአደረጉ፣ አድራጊወች (ወ)
- ገባሪት= የምታደርግ፣ የአደረገች፣ አድራጊ
- ገባርያት= የሚያደርጉ፣ የአደረጉ፣ አድራጊወች (ሴ)

- ገባሪ ይገብር ይረክብ ንዋይ፣
  ነዋሚ ይነውም ይነጼር ራዕይ፣
  ተንባሊ ይተንብል ይረክብ ሲሳይ።

ተንበለ=ለመነ

- ተንባሊ=የለመነ፤የሚለምን፤ለማኝ
- ተንባልያን=የለመኑ፤የሚለምኑ፤ለማኞች(ወ)
- ተንባሊት=የለመነች፤የምትለምን፤ለማኝ
- ተንባልያት=የለመኑ፤የሚለምኑ፤ለማኞች(ሴ)

- ባራኪ=የመረቀ፣የሚመርቅ፣መራቂ
- ባራኪያን=የመረቁ፣የሚመርቁ፣መራቂወች (ወ)
- ባራኪት= የመረቀች፣የምትመርቅ፣ መራቂ
- ባራኪያት =የመረቁ፣የሚመርቁ፣መራቂወች (ሴ)

ዴገነ=ተከተለ

- ዴጋኒ=የተከተለ፣የሚከተል፣ተከታይ
- ዴጋንያን= የተከተሉ፣የሚከተሉ፣ተከታዮች（ወ）
- ዴጋኒት= የተከተለች፣የምትከተል፣ተከታይ
- ዴጋንያት=የተከተሉ፣የሚከተሉ፣ተከታዮች（ሴ）

ከሕለ=ቻለ

- ከሀሊ=የቻለ፤የሚችል፤ቻይ
- ከሀሊያን =የቻሉ፤የሚችሉ፤ቻዮች (ወ)
- ከሀሊት= የቻለች፤የምትችል፤ቻይ
- ከሀልያት =የቻሉ፤የሚችሉ፤ቻዮች (ሴ)

ጠመረ=ጻፈ

- ጠማሪ=የጻፈ፣የሚጽፍ፣ጻሀፊ
- ጠማሪያን=የጻፉ፣የሚጽፉ፣ጻሀፊወች（ወ）
- ጠማሪት=የጻፈች፣የምትጽፍ፣ጻሀፊ
- ጠማሪያት=የጻፉ፣የሚጽፉ፣ጻሀፊወች（ሴ）

1.2 ሳድስ ውስጠ *ዘ*

- **ግሱ የቅርጽ ለውጥ ካመጣ በኋላ የመጨረሻዋ ፊደል ስድስተኛ/ሳድስ/ስለምትሆን ነው።**
- ትርጉሙም እንደ ግሡ የሚወሰን ሆኖ ባጠቃላይ ግን "**እንዲህ የተደረገ** " የሚል ይሆናል።
- ምሳሌ የተገደለ፣የተመሰገነ...

ከዚህ ቀጥለን የስምንቱን አርስተ ግሦች ሳድስ ውስተ ዘ እንመለከታለን።

ቀተለ

- ቅቱል=የተገደለ (ለ አንድ ነጠላ ቁጥር ወንድ)
- ቅቱላን=የተገደሉ (ለብ. ወ)
- ቅትልት=የተገደለች (ለአንዲት ነጠላ ቁጥር ሴት)
- ቅቱላን=የተገደሉ （ለብ. ሴ）

ቀደሰ

- ቅዱስ=የተመሰገነ፣የነጻ፣የተለየ
- ቅዱሳን= የተመሰገኑ፣የነጹ፣የተለዩ （ወ）
- ቅድስት= የተመሰገነች፣የነጻች፣የተለየች
- ቅዱሳት= የተመሰገኑ፣የነጹ፣የተለዩ （ሴ）

ገብረ

- ግቡር=የተደረገ
- ግቡራን=የተደረጉ （ወ）
- ግብርት=የተደረገች
- ግቡራት= የተደረጉ （ሴ）

ተንበለ

- ትንቡል=የተለመነ
- ትንቡላን=የተለመኑ （ወ）
- ትንብልት=የተለመነች
- ትንቡላት =የተለመኑ （ሴ）

ባረከ

- ቡሩክ=የተመረቀ
- ቡሩካን=የተመረቁ（ወ）
- ቡሩ(ር)ክት=የተመረቀች
- ቡሩ(ር)ካት=የተመረቁ（ሴ）

ዶገነ

- ዲጉን= ሌሎች የሚከተሉት
- ዲጉናን= ሌሎች የሚከተሏቸው （ወ）
- ዲግንት= ሌሎች የሚከተሏት
- ዲጉናት= ሌሎች የሚከተሏቸው （ሴ）

ከህለ

- ከሁል=የተቻለ
- ከሁላን=የተቻሉ（ወ）
- ከህልት=የተቻለች
- ከሁላት=የተቻሉ（ሴ）

ጠመረ

- ጡሙር=የተጻፈ
- ጡሙራን=የተጻፉ（ወ）
- ጡሙርት=የተጻፈች
- ጡሙራት=የተጻፉ（ሴ）

2. አርእስት

- የሁሉም ቃል መነሻ ስለሆነ ነው።
- እንደ አንዳንድ መጽሀፍት ገለጻ አሁን እኛ እንደምንለው አርዕስት የግሥ ንዑስ አንቀጽ ሳይሆን ግሱ ነው ከአርዕስቱ የሄደ ነው በማለት የቃላት ኹሉ መገኛ ነው በማለት የሚያብራሩ ሲሆን ይኸውም **አርዕስት** ከግስ ይልቅ ጾታንና ቁጥርን ስለማይለይ "**የሁሉም ቃል መነሻ ነው**" በሚለው ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ።
- ትርጉሙም እንደቃሉ የሚለያይ ሆኖ "**ማድረግ** " የሚል ጠቅላላ ትርጉም ይይዛል፣፣
- ምሳሌ፡- **መግደል፣ ማመስገን፣ መዘመር**

በአርስት ጊዜ ሁለተኛቸውን ሣልስ የሚያደርጉ

- ቀቲል/ቀቲሎት=መግደል
- ገቢር/ገቢሮት=ማድረግ/መስራት
- ክሂል/ክሂሎት=መቻል

በአርስት ጊዜ ሁለተኛቸውን ሳድስ የሚያደርጉ

- ቀድሶ/ቀድሶት➔ማመስገን
- ተንብሎ/ተንብሎት➔መለመን
- ባርኮ/ባርኮት➔መመረቅ
- ዴግኖ/ዴግኖት➔መከተል
- ጦምሮ/ጦምሮት➔መጻፍ

የቀተለ አርእስት ንዑስ አንቀጽ እርባታ

- ቀቲል/ቀቲሎት= መግደል

- ቀቲልየ/ቀቲሎትየ→ መግደሌ
- ቀቲልነ/ቀቲሎትነ→ መግደላችን
- ቀቲልከ/ቀቲሎትከ → መግደልህ
- ቀቲልኪ/ቀቲሎትኪ → መግደልሽ
- ቀቲልክሙ/ቀቲሎትክሙ → መግደላችሁ
- ቀቲልክን/ቀቲሎትክን → መግደላችሁ
- ቀቲሉ/ቀቲሎቱ → መግደሉ
- ቀቲላ/ቀቲሎታ → መግደሏ
- ቀቲሎሙ/ቀቲሎቶሙ → መግደላቸው
- ቀቲሎን/ቀቲሎቶን → መግደላቸው

3. ቦዝ

- ቦዝ ማለት ከስሙ እንደምንረዳው የፈዘዘ ማሰሪያ አንቀጽነቱን ያጣ እንደ ማለት ነው።
- የድርጊት ገላጭነት ሚናውን ባያጣም ነገር ግን የአረፍተ ነገር መቋጫ በምሆን አያስርልንም።
- ትርጉሙም "**አድርጎ**" የሚል ይሆናል።
- ምሳሌ፡- ገድሎ፣ መርቆ፣ ለምኖ ፣ ችሎ…

በቦዝ ጊዜ ሁለተኛቸውን ሣልስ የሚያደርጉ

- ቀቲሎ=ገድሎ
- ገቢሮ=አድርጎ
- ክሂሎ=ችሎ
- ተንቢሎ=ለምኖ

በቦዝ ጊዜ ሁለተኛቸውን ሳድስ የሚያደርጉ

- ቀድሶ=አመስግኖ
- ባርኮ=አመስግኖ
- ዴግኖ=ተከትሎ
- ጦምሮ=ጽፎ

የቦዝ አንቀጽ አዕማድ እርባታ

- ቀቲሎ(ገድሎ)
- ተቀቲሎ(ተገድሎ)
- አቅቲሎ(አስገድሎ)
- ተቃቲሎ(ተገዳድሎ)
- አስተቃቲሎ(አገዳድሎ)

ቦዝ አንቀጽ በአስሩ መራህያን ሲረባ

- 1ኛ እና 2ኛ መደብ የመጨረሻውን ፊደል ግዕዝ አድርጎ (የ"አነ" ግን ሳድስ እንደሆነ) የተለመዱትን ቅጥያወች መጨመር ነው።
- 3ኛ መደብ ላይ "ኡ፣ አ፣ አሙ፣ አን" ን ለውእቱ፣ይእቲ፣ውእቶሙ እና ውዕቶን እንደ ቅደምተከተላቸው መጨመር ነው።

ከሰተ=ገለጠ

- **ከሲትየ=ገልጨ**
- ከሲተነ=ገልጠን
- ከሲተከ= ገልጠህ
- ከሲተኪ=ገልጠሽ
- ከሲተክሙ=ገልጣችው
- ከሲተክን= ገልጣችው
- ከሲቶ=ገልጦ
- ከሲታ=ገልጣ
- ከሲቶሙ=ገልጠው
- ከሲቶን=ገልጠው

ምሳሌያት፡-

- ፈቂድየ መጻእኩ
- አፍቂርየ አውሰብኩ
- ኅዲገኪ ሖርኪ
- አሚኖ ክህደ
- ወዲቆ ተንሥአ
- ✓ ወዲቀከ ትትነሳእ
- ✓ ቀቲሎ ሀለወ
- ቀቲላኒ ይእቲ
- ቀቲሎኒ
- ቀቲላ ኪያየ
- ✓ ሰጊዶሙ ይዜምሩ
- ❖ አርሚምየ እሔር
- ❖ ገቢረነ ንስክብ

- ኅዲጎ ተስዐ ነገደ ወረደ ወልድ
- አፍቂሮ ብእሲቶ
- መኒኖ ዐለመ
- ወመጺኦ መምህሮሙ ተንሥኡ አርድእት
- ወሰሚኦ ሄሮድስ ንጉሥ ደንገጸ ወተሀውከ
- አይቴ ተሐውር ነሲአከ ለንዋይየ
- ወበዊኦሙ ውስተ ቤት ረከብዎ ለሕፃን ምስለ ማርያም እሙ

፫) ጸዋትወ አንቀጽ (ስረይ ግሥ) Irregular Verbs)

- ግሥን ሁሉ በየወገኑ (በየአመሉ) ለይተን እንድናረባ የሚያስተምረን ክፍል ጸዋትው ይባላል።
- በእርባታቸው ከስምንቱ አርእስት የተለዩና እነርሱን ለመሰሉ ሁሉ የእርባታ መጠየቂያ ለሚሆኑ ግሦች የተሰጠ ሥያሜ ነው።
- **ስረይ ግሥ** የተባለበት ምክንያት አንድ ስረይ ግሥ እንደ ርእስ (አለቃ) እንዳይቆጠር አለቃ አለው፤ እንደ ሠርዌ እንዳይቆጠር ከአለቃው የተለየ ነው(እንደ አለቃው ሙሉ በሙሉ አይሄድም) ።
- ንዑስ ርእስ (ትንሽ አለቃ) እንደማለት ነው። ሦስት ዓይነት ፀዋትው የግሥ እርባታ ሕግጋት አሉ።

✓ሦስት ዓይነት ፀዋትው የግሥ እርባታ ሕግጋት አሉ።

እነርሱም፦

1. ‘ሀ’ እና ‘አ’ ያሉባቸው አንድ ወገን / አመል/
2. ‘ወ’ ያለባቸው ሌላ ወገን /አመል/
3. ’የ’ ያለባቸው ሦስተኛ ወገን /አመል/

የ 'ሀ' እና የ'አ' አመል

፩, በቀተለ ቤት ሲገኙ የሚያመጡት ለውጥ

✓ በመነሻ ሲገኙ፡- በትንቢት አንቀጽ አሥራውን ግእዝ ያደርጉታል። ሌላ ለውጥ የለውም።

ምሳሌ፡-

- **ሐለመ**--- የሐልም፡ ይሕልም፡ ይሕልም፡ ሐሊም/ሐሊሞት
- **አነመ**--- የአንም፡ ይእንም፡ ይእንም፡ አኒም/አኒሞት
- **ኀዘነ**--- የኀዝን፡ ይኀዝን፡ ይኀዝን፡ ኀዚን/ኀዚኖት

✓ <u>በመካከል ሲገኙ</u>፡- **ሦስት አይነት ለውጥ ያመጣሉ።**

1. ትንቢት አንቀጽን ፍጹም ሳድስ ያደርጉታል።
2. በዘንድና በትእዛዝ ቅድመ መድረሻውን ግእዝ ያደርጉታል።
3. የአርእስቱን መነሻ ሳድስ ያደርጉታል።

ምሳሌ፡-

- መሐለ--- ይምሕል፡ ይምሐል፡ ይምሐል፡ምሒል/ሎት
- ሰአለ--- ይስእል፡ ይስአል፡ ይስአል፡ ስኢል/ሎት
- ሰዐረ--- ይስዕር፡ ይስዐር፡ ይስዐር፡ ስዒር/ሮት

❑ **ማስታወሻ፡-** ‘ሀ’ እና ‘አ’ በቀተለ ቤት በመድረሻ አይገኙም።

፩, በቀደሰ ቤት የሚያመጡት ለውጥ

✓ በመነሻ ሲገኙ፡- በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ አሥራውን ግእዝ ያደርጉታል።

ምሳሌ፡-

- ሐወጸ--- ይሔውጽ፡ የሐውጽ፡ የሐውጽ፡ ሐውጾ/ጾት
- ዐመጸ--- ይዔምጽ፡ የዐምጽ፡ የዐምጽ፡ ዐምጾ/ጾት
- ሀየለ--- ይሄይል፡ የሀይል፡ የሀይል፡ ሀይሎ/ሎት

✓ **በመድረሻ ሲገኙ፡-** **ሦስት ቀለማት ባሉት የቀደሰ ቤት መድረሻ ሲገኙ ለውጥ አያመጡም።**

- ቀለማቱ አራትና ከዚያ በላይ ከሆኑ ግን በትንቢት፣ በዘንድና ትእዛዝ አናቅጽ ቅድመ መድረሻውን ራብዕ ያደርጋሉ።

ምሳሌ፡-

- ጸውዐ--- ይጼውዕ፡ ይጸውዕ፡ ይጸውዕ፡ ጸውዖ/ዖት
- ተፈሥሐ--- ይትፌሣሕ፡ ይትፈሣሕ፡ ይትፈሣሕ፡ ተፈሥሖ/ሖት

❑ **ማስታወሻ፡- 'ሀ' እና 'አ' በቀደሰ ቤት በመካከል አይገኙም።**

፫, በገብረ ቤቶች ላይ የሚያሳዩት ለውጥ

በመነሻ ሲገኙ

«ሀ» እና «ሐ» በገብረ ቤቶች በመነሻ ሲገኙ በትንቢት አንቀጽ አሥራው ግእዝ ይሆናል።

ምሣሌ፡-አምነ	የአምን	ይእመን	ይእመን	አሚን/ኖት
ኀልቀ	የኀልቅ	ይኀለቅ	ይኀለቅ	ኀሊቅ/ቆት
ዐርገ	የዐርግ	ይዕረግ	ይዕረግ	ዐሪግ/ጎት

«ሀ» እና «ሐ» በገብረ ቤቶች በመካከል አይገኙም።

«ሀ» እና «ሐ» በገብረ ቤቶች በመድረሻ ሲገኙ በዘንድ እና ትእዛዝ አናቅጽ ቅድመ መድረሻውን ራብዕ ቀለም ያደርጉታል።

ምሣሌ፡- በልዐ	ይበልዕ	ይብላዕ	ይብላዕ	በሊዕ/በሊዖት
በጽሐ	ይበጽሕ	ይብጻሕ	ይብጻሕ	በጺሖ/ሖት
ፈትሐ	ይፈትሕ	ይፍታሕ	ይፍታሕ	ፈቲሕ/ሖት

፬ በተንበለ ቤቶችበመነሻ ሲገኙ የሚያሳዩት ለውጥ

አንድ «ሀ» ወይም «አ» ብቻ ሲሆን

በዚህ ጊዜ አሥራው ከትንቢት እስከ ትእዛዝ አንቀጽ ድረስ ራብዕ ይሆናሉ።

ምሣሌ፡-አመድበለ	ያመደብል	ያመድብል	ያመድብል	አመድብሎ/ሎት
አመከነየ	ያመከኒ	ያመክኒ	ያመክኒ	አመክንዮ/ዮት
አንቀልቀለ	ያንቀለቅል	ያንቀልቅል	ያንቀልቅል	አንቀልቅሎ/ሎት

መነሻውም ድኅረ መነሻውም የ«ሀ» እና «አ» ዘር ሲሆን በትንቢት አስራው ግእዝ ይሆናል።በዘንድ እና ትእዛዝ ደግሞ ራብዕ ይሆናሉ።

ምሣሌ፡-አእመረ	የአምር	ያእምር	ያእምር	አእምሮ/ሮት
አእተተ	የአትተ	ያእትት	ያእትት	አእትቶ/ቶት
አእኰተ	የአኵት	ያእኵት	ያእኵት	አእኵቶ/ቶት

«ሀ» እና «አ» በተንበለ ቤቶች በመካከል እና በመድርሻ ሲገኙ ለውጥ አያመጡም።

፫. የባረከ ቤት

✓አራት ቀለም ባለው (ይኸውም የ"*ማሕረከ*" የሆኑት) ሁልጊዜ በመካከል «ሀ» ወይም «አ» ይገኛሉ።

✓በእርባታ ጊዜም በትንቢት አንቀጽ ድኅረ መነሻውን ግእዝ በዘንድ እና በትእዛዝ ራብዕ ያደርጋሉ።

ምሣሌ፡-

- **ማህረከ** ይመሀርክ ይማህርክ ይማህርክ ማህርኮ/ኮት
- **ጻዕደወ** ይጻዐዱ ይጻዕዱ ይጻዕዱ ጻዕድዎ/ዎት
- **ጻሕየየ** ይጻሐይይ ይጻሕይይ ይጻሕይይ ጻሕይዮ/ዮት

፮. በክህለ ቤቶችም ሁልጊዜ መካከሉ «ሀ» ወይም «አ» አለባቸው።

ምሣሌ፡-

- ✓ቄቅሐ ይቄቅሕ ይቄቅሕ ይቄቅሕ ቄቅሖ/ሖት
- ✓ቶስሐ ይቶስሕ ይቶስሕ ይቶስሕ ቶስሖ/ሖት
- ✓ኖሠሠ ይኖሥሥ ይኖሥሥ ይኖሥሥ ኖሥሦ/ሦት
- ✓ርኅቀ ይርኅቅ ይርኅቅ ይርኅቅ ርኂቅ/ቆት

❑**ማስታወሻ**፡- «ሀ» እና «አ» ከላይ ካየናቸው ውጭ ባሉ አርእስቶች ሲገኙ ለውጥ አያሳዩም።

ማስታወሻ፡- ፩ ማንኛውም በሳብዕ የሚጀምር ግስ በውስጡ «ወ» አለው። በኀምስ የሚጀምር ግስም በውስጡ «የ» አለው። ስለዚህም ሁለት ቀለማት ያላቸውንና በኃምስ እና በሳብዕ የሚጀምሩ ግሶችን በምናረባ ጊዜ በውስጥ ያሉትን «ወ» እና «የ» በማውጣት ይሆናል።

ምሣሌ፡- «ቆመ» ን ስነናረባ «ቀወመ» እንደ ሆነ አድርገን ነው።

ቆመ	ይቀውም	ይቁም	ይቁም	ቀዊም/ሞት
ፆረ	ይፀውር	ይፁር	ይፁር	ፀዊር/ሮት
ሤመ	ይሠይም	ይሢም	ይሢም	ሠዪም/ሞት
ኤለ	የአይል	ይኢል	ይኢል	አዪል/ሎት
ኄሰ	የኀይስ	ይኂስ	ይኂስ	ኀዪስ/ሶት

፪ በእርባታ ጊዜ የቀተለን ከቀደሰ የቀደሰን ከቀተለ እየደባለቁ የሚረቡ ግሶች አሉ። እነርሳቸውም ቱሱሓን ይባላሉ። ከዚህም ሌላ ህገ ወጦች አሉ። ምሳሌ፡- ሐገገ ይሔግግ ይሕግግ ይሕግግ ሐጊግ/ጎት

አንስሐስሐ ያንሰሕስሕ ያንሳሕስሕ ያንሳሕስሕ አንሳሕስሖ/ሖት

የ«ወ» አመል

1, በገቢር ግሶች ላይ ያለው ለውጥ

በመነሻ ሲገኝ

«ወ» በቀተለ፣ በገብረና በከሀለ ቤቶች በመነሻ ሲገኝ በዘንድ እና በትእዛዝ ይጠፋል።ከ«ወ» ቀጥሎ ያለው የ«ሀ» ወይም የ«አ» ቤት ከሆነ ደግሞ አሥራው ግእዝ ይሆናሉ።

ምሣሌ፡-	ወረደ	ይወርድ	ይረድ	ይረድ	ወሪድ/ዶት
	ወድቀ	ይወድቅ	ይደቅ	ይደቅ	ወዲቅ/ቆት
	ውኅዘ	ይውኅዝ	የኅዝ	የኅዝ	ውኂዝ/ዞት
	ወደየ	ይወዲ	ይደዩ	ይደዩ	ወዲዩ/ዮት
	ወለደ	ይወልድ	ይለድ	ይለድ	ወሊድ/ዶት

«ወ» በቀደሰ እና በተንበለ ቤቶች በመነሻ ሲገኙ አይጎረዱም።

ምሳሌ፡-	ወደሰ	ይዌድስ	ይወድስ	ይወድስ	ወድሶ/ሶት
	ወሰከ	ይዌስክ	ይወስክ	ይወስክ	ወስኮ/ኮት
	ወለጠ	ይዌልጥ	ይወልጥ	ይወልጥ	ወልጦ/ጦት
	ወርዘወ	ይወረዙ	ይወርዙ	ይወርዙ	ወርዝዎ/ዎት

ማስታወሻ፡- በሌሎች ግሶች በመነሻ ላይ አይገኝም።

በመካከል ሲገኝ፡- ራሱን ኀርዶ ግእዝ የነበረውን ፊደል ወደ ሳብዕ ይለውጣል። ስለዚህም በሳብዕ የሚጀምር ግሥ ሁሉ በውስጡ ‘ወ’ አለበት።

ምሳሌ፡- ቀወመ--- ቆመ　　　ሐወረ--- ሖረ

　　ነወለወ--- ኖለወ　　　ነወመ--- ኖመ

በመድረሻ ሲገኝ፡-

1. በገቢር ግሦች በመድረሻ ሲገኝ በካልዕይ፣ ዘንድና ትእዛዝ አናቅጽ ፊቱ ያለውን ፊደል ወደ ካዕብ ለውጦ ራሱን ይኀርዳል።

ምሳሌ፡- ፈነወ--- ይፌኑ፡ ይፈኑ፡ ይፈኑ

ነቀወ-- ይነቁ፡ ይንቁ፡ ይንቁ

ለበወ--- ይሌቡ፡ ይለቡ፡ ይለቡ

ዘረወ--- ይዘሩ፡ ይዝሩ፡ ይዝሩ

ወርዘወ--- ይወረዙ፡ ይወርዙ፡ ይወርዙ

ማስታወሻ፡ ‘ወ’ በግሥ መድረሻ ላይ ደጊመ ቃል ሲሆን አይኀርድም።

ምሳሌ፡- ከወወ--- ይከውው፡ ይከውው፡ ይከውው

　　ዄወወ--- ይዄውው፡ ይዄውው፡ ይዄውው

2. በተገብሮ ግሦች ላይ በመድረሻ ሲገኝ ራሱን ጎርዶ ፊቱ ያለውን ፊደል ወደ ሳብዕ ይለውጣል። በተገብሮ ግሦች ‘ተ’ ን ተከትለው ያሉት ፊደላት “**ተ፣ ሠ፣ ሰ፣ ዘ፣ ደ፣ ጸ፣ፀ፣ ጠ**” ከሆኑ ‘ተ’ ትዋጣለች።

- **ምሳሌ፡-**

- ተፈነወ--- ይትፌኖ፡ ይትፈኖ፡ ይትፈኖ
- ተደመረ--- ይዴመር፡ ይደመር፡ ይደመር
- ተሰፈወ--- ይሴፎ፡ ይሰፎ፡ ይሰፎ፡ ይሰፎ
- ተሠገወ--- ይሤጎ፡ ይሠጎ፡ ይሠጎ
- ተፀወነ ይፄወን፤ይፀወን፤ይፀወን
- ተሰብሐ ይሴባሕ፤ይሰባሕ፤ይሰባሕ

አዕማድ

- አዕማድ (አምስቱ ማዕረጋት) ለግስ እርባታ ሁሉ መነሻ እና መቋቋሚያ ወይም የግስን ፆታ፤የአንቀጽን እርባታ በየቤቱና በየሠራዊቱ ፀንቶ እንዲነገር የሚወስኑ እና ለይተው የሚመሩ ስለሆኑ አዕማድ ወይም አዕማደ ግሥ ተብለዋል፡፡
- እነዚህ አምስቱ የግሥ ማዕረጋት የሚከተሉት ናቸው፡፡

፩. አድራጊ ዐምድ (ገቢረ)

፪. ተደራጊ ዐምድ (ተገብሮ)

፫. አስደራጊ ዐምድ (ገቢር)

፬. ተደራራጊ ዐምድ (ተገብሮ)

፭. አደራራጊ ዐምድ (ገቢር)

❑ምሳሌ ፦

- ቀተለ(ገደለ) አድራጊ ዐምድ
- አቅተለ(አስገደለ) አስደራጊ ዐምድ
- ተቀትለ(ተገደለ) ተደራጊ ዐምድ
- ተቃተለ(ተገዳደለ) ተደራራጊ ዐምድ
- አስተቃተለ(አገዳደለ) አደራራጊ ዐምድ

- ግሦች በአምስቱ አዕማድ ሲረቡ ለእርባታቸው **ህፀፅ እና ምልዐት** አለው፡፡
- በምልዐት ሲረቡ አምስቱንም ደረጃ ይወጣሉ፡፡ በህፀፅ ሲረቡ ከአምስት ያነሰ ደረጃን ይወጣሉ፡፡

ደረጃ	አድራጊ	አስደራጊ	ተደራጊ	ተደራራጊ	አደራራጊ
፩	ቀተለ	አቅተለ	ተቀተለ	ተቃተለ	አስተቃተለ
፪	ፈለሰ	አፍለሰ		ተፋለሰ	አስተፋለሰ
፫	ሐነጸ	አሕነጸ	ተሐነጸ		
፬	ዘነመ	አዝነመ			
፭	ኮነ				

- ከላይ ባየናቸው አዕማድ ላይ በመነሻ የምናገኛቸው ባዕዳን ፊደላት “ተ፤አ፤አስተ” ልማድ ይባላሉ፡፡

❑ “ተ” የመደረግ፤የመደራረግ ልማድ ነው፡፡ነገር ግን ተወከፈ፤ተዘከረ ያለውን የሚመስል ግሥ የማድረግ ሲሆን ይገኛል፡፡

❖ “አ” የማስደረግ ልማድ ሲሆን የመደረግና የማድረግ ሆኖ ይገኛል

- ምሳሌ፡- አየድዐ ያየድዕ፤ያየድዕ፤ያየድዕ

❖ “አስተ” የማደራረግ ልማድ ሲሆን የመደረግ፤የማድረግ፤የማስደረግ ሆኖ ይገኛል፡፡

- ምሳሌ፡- አስተርአየ(አየ፤አሳየ) ፤ አስተብቍዐ(ማለደ)

ሀ. አድራጊ ዐምድ

- ራሱን ችሎ በሀላፊ አንቀጽ የሚነገር የአዕማድ ሁሉ መሠረት ነው፡፡
- ምሳሌ ፡- ቀተለ፤ቀደሰ፤ተንበለ
- አድራጊ ዐምድ ግእዝን፤ራብዕን፤ኃምስን፤ሳብዕን ይስባል፡፡
- ምሳሌ ፡-
- ሰበኩ ሐዋርያት ወንጌለ
- ርእየ አንበሳ ውስተ ሐቅል
- ረከበ አርዌ ውስተ ገዳም

ለ. አስደራጊ ዐምድ

- በመነሻው ላይ ባዕድ ፊደል ‘‘አ’’ ን በመጨመር ከአድራጊ ግሥ ይመሰረታል
- ምሳሌ፡-
- ሐይወ አሕየወ
- ጸሐፈ አጽሐፈ
- አስደራጊ ዐምድ ሁለት ግእዝን ይስባል፡፡
- ምሳሌ፡- ያፈቅርዎ ሕዝብ ለባዕል ዘአብልዐ ነዳየ ኀብስተ

ሐ. አደራራጊ ዐምድ

- ❑በመነሻው ላይ ባዕድ ፊደል “አስተ” ን በመጨመር ከአድራጊ ዐምድ ይመሰረታል፡፡
- ምሳሌ፡- ቀተለ አስተቃተለ
- ❑አደራራጊ ዐምድ “**ምስለ**”ን አጫፍሮ ስምን ይስባል።
- ምሳሌ፡- አስተቃተለ ሳሙኤል ሳኦልሃ ምስለ አጋግ

መ. ተደራጊ ዐምድ

- በመነሻ ላይ “ተ” ን በመጨመር ከአድራጊ ዐምድ ይመሰረታል፡፡
- ምሳሌ፡- ተቀትለ፤ተቀደሰ
- ተደራጊ ዐምድ ተገብሮ ያደርጋል፡፡
- ምሳሌ፡- ተሐንጸ ቤት

ሠ. ተደራራጊ ዐምድ

- ❑በመነሻው ላይ ባዕድ ፊደል “ተ” ን በመጨመር፤ድኅረ መነሻውን ራብዕ በማድረግ ከአድራጊ ዐምድ ይመሰረታል፡፡
- ምሳሌ፡- ተቃተለ፤ተባረከ፤ተናገረ
- ❑ተደራራጊ ዐምድ እርስ በእርሱ በሚደረግ ግብር እየገባ ይሠራል፡፡
- ምሳሌ፡-
- ተቃተለ ዳዊት ምስለ ጎልያድ
- መላእክት ተናገሩ ምስለ ጎልያድ

ማስታወሻ፡- የ "ተ" እና የ "ጠ" ግሦች የሩቂቱ ሴት ውስጠ ዘ መድረሻ ፊደሉ (ት ወይም ጥ) ይውጣል፡፡

- **ምሳሌያት ፡-**

- ምውት እንጅ ምውትት አይልም።
- ፍልጥ እንጅ ፍልጥት አይልም።

የ ‘የ’ አመል

- **<u>በግሥ መነሻ ላይ ሲገኝ</u>** የእርባታ ለውጥ አያስከትልም።

ምሳሌ፡- የበበ--- ይዬብብ፡ ይየብብ፡ ይየብብ

- **<u>በግሥ መካከል ሲገኝ</u>**፡- ራሱን ጎርዶ በቀዳማይ መነሻውን ጎምስ፣ በዘንድና በትእዛዝ መካከሉን ሣልስ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-

- ሤመ--- ይሠይም፡ ይሢም፡ ይሢም
- ኄሰ--- የኅይስ፡ ይኂስ፡ ይኂስ

በመድረሻ ሲገኝ፡-

1, በገቢር ግሥ በመድረሻ ላይ ሲገኝ ከትንቢት አንቀጽ እስከ ትእዛዝ አንቀጽ ድረስ ራሱን ጎርዶ ፊቱ ያለውን ፊደል ሣልስ ያደርጋል። የአርእስቱንም መካከል ሳድስ ያደርጋል።

ምሳሌ፡- በቀተለ ቤት ገነየ--- ይገኒ፡ ይግኒ፡ ይግኒ፡ ገንይ/ዮት

በቀደሰ ቤት ጸለየ--- ይጼሊ፡ ይጸሊ፡ ይጸሊ፡ ጸልዮ/ዮት

በገብረ ቤት ሰትየ--- ይሰቲ፡ ይስቲ፡ ይስቲ፡ ሰትይ/ዮት

በባረከ ቤት ሣቀየ--- ይሣቂ፡ ይሣቂ፡ ይሣቂ፡ ሣቅዮ/ዮት

'የ' በመድረሻ ደጊመ ቃል በሆነበት አይጎርድም።

ምሳሌ፡- ጐየ/ጐየየ--- ይጐይይ፡ ይጒየይ፡ ይጒየይ፡ ጐይዮ/ዮት

ጸሀየየ--- ይጸሀይይ፡ ይጸሀይይ፡ ይጸሀይይ፡ ጸሀይዮ/ዮት

- በቦዝ አንቀጽ እርባታ ጊዜ ‘የ’ ቅድመ መድረሻውን ሣልስ በማድረግ ፋንታ ሳድስ ያደርጋል።

ምሳሌ፡-

- ቀቲል--- ቀቲሎ(ቦዝ)
- ሠነየ--- ሠንዮ
- ጸለየ--- ጸልዮ

ምሳሌ፡-

- ተከረየ--- ይትከረይ፡ ይትከረይ፡ ይትከረይ፡ ተከርዮ/ዮት
- ተሌለየ--- ይትሌለይ፡ ይተሌለይ፡ ይትሌለይ፡ ተሌልዮ/ዮት
- ተሴሰየ--- ይሴሰይ፡ ይሴሰይ፡ ይሴሰይ፡ ሴስዮ/ዮት

ዝርው

- ዝርው የተባሉ ከአርዕስትና ከሥራዊት ስም የሌላቸው ቀለማት “ቈ” “ኰ” “ጐ” “ኈ” ን መነሻ፣ መሀከል፣ መድረሻ ያደረጉ ግሦች ናቸው፡፡ እነዚህም በየራሳቸው በየጠባያቸው ይረባሉ፡፡
- ምሳሌያት፡-

ሀ. ኈለቈ (ቆጠረ)፡ ይኄልቍ፤ይኈልቍ፤ይኈልቍ

ለ. ለሐኰ (ሠራ)፡ ይልሕኵ፤ ይልሐኵ፤ ይልሐኵ

ሐ.ጐየ (ሸሸ)፡ ይጐይይ፤ይጕይይ፤ይጕይይ(ይጕየይ)

መ.ጕሕቈ

ሠ.ጐጕዐ

ረ. ጐንደየ

ሰ.ጐድአ

ቀ. ቈቍዐ

2. ዝርዝር እርባታ

- የትኛው መራሒ (አድራጊው) ከየተኛው መራሒ (ተደረጊው) ላይ ድርጊት እንደፈጸመ የሚያሳይ፡፡
- የተሳቢውን (የተደራጊውን) ማንነት የሚያሳውቁን በግሱ መድረሻ ላይ በምእላድነት የሚገቡ ፊደላት ናቸው፡፡
- እነርሱም ግሳውያን የተሳቢ አጸፋ ተውላጠ ስም ይባላሉ፡፡

የተሳቢ አጻፋ ተውላጠ ስሞች

	ጾታ	ብዙ	ነጠላ
፩ኛ መደብ		ነ	ኒ
፪ኛ መደብ	ተባዕት	ክሙ	ከ
	አንስት	ክን	ኪ
፫ኛ መደብ	ተባዕት	ዎሙ፣ሆሙ፣ዮሙ፣ኦሙ	ዎ፣ሁ፣ ሆ፣ዮ፣ኦ
	አንስት	ዎን፣ሆን፣ዮን፣ኦን	ዋ፣ሃ፣ያ፣አ

=ኒ አነ

=ነ ንሕነ

=ከ አንተ

=ኪ አንቲ

=ክሙ አንትሙ

=ክን አንትን

=ዎ፤ሆ፤ዮ፤ኦ (ሳብእ ማድረግ)
=ዋ፤ሃ፤ያ፤ኣ (ራብእ ማድረግ)
=ዎሙ፤ሆሙ፤ዮሙ፤ኦሙ (ሳብእ+ሙ ማድረግ)
=ዎን፤ሆን፤ዮን፤ኦን (ሳብእ+ን ማድረግ)

ውእቱ
ይእቲ
ውእቶሙ
ውእቶን

የዝርዝር እርባታን ለማግኘት ቅደም ተከተል በቀዳማይ አንቀጽ ጊዜ

1. መጀመሪያ የተሰጠውን ግስ ወደ አድራጊው መራሒ ማርባት
2. ከዚያ ቅጥያ ሲጨምር **የቅርጽ ለውጥ የሚያመጣ** መራሒ ከሆነ መለወጥ
3. ተደራጊው ማን እንደሆነ የሚገልጽ ቅጥያ መጨመር

ለቅደም ተከተሉ ምሳሌ ወንዶች ገዙኝ ለማለት

- ግስ=አጥረየ

1. አጥረ<u>ዩ</u>
2. ውእቶሙ የቅርጽ ለውጥ አያመጣም
3. አጥረዩ<u>ኒ</u>

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ እያንዳንዱ መራሒ ከሌላው መራሒ ሲተገብር ሁሉን እንደ

- ❖ 1ኛና በተለይ 2ኛ መደብ መራሕያን ከራሳቸው መደብ ላይ አይተገብሩም

1ኛ መደብ፡2*8=16

2ኛ መደብ፡4*6=24

3ኛ መደብ፡4*10=40

16+24+40=80

አነ እንዘ ይገብር
አነ ሲያደርግ

- ሰከልኩከ
- ሰከልኩኪ
- ሰከልኩክሙ
- ሰከልኩክን
- ሰከልክዎ
- ሰከልክዋ
- ሰከልክዎሙ
- ሰከልክዎን

ንሕነ
ሰከልና…

- ሰከልናከ
- ሰከልናኪ
- ሰከልናክሙ
- ሰከልናክን

- ሰከልናሁ
- ሰከልናሃ
- ሰከልናሆሙ
- ሰከልናሆን

ንሕነ
ሁለተኛ መንገድ ሰከልነ...

- ሰከልነከ
- ሰከልነኪ
- ሰከልነክሙ
- ሰከልነክን
- ሰከልኖ
- ሰከልና
- ሰከልኖሙ
- ሰከልኖን

አንተ
ቀተልከ...

- ሰከልከኒ
- ሰከልከነ
- ሰከልኮ
- ሰከልካ
- ሰከልኮሙ
- ሰከልኮን

አንተ

ሁለተኛ አካሄድ ቀተልካ...

- ሰከልካኒ
- ሰከልካነ
- ሰከልካሁ
- ሰከልካሃ
- ሰከልካሆሙ
- ሰከልካሆን

አንቲ ሰከልከ…

- ሰከልከኒ
- ሰከልከነ
- ሰከልከዮ
- ሰከልከያ
- ሰከልከዮሙ
- ሰከልከዮን

አንቺ
ሁለተኛ አካሄድ ሰከለከ...

- ሰከለክኒ
- ሰከለክነ

- ሰከለክዮ
- ሰከለክያ
- ሰከለክዮሙ
- ሰከለክዮን

አንትሙ

- ሰከልክሙኒ
- ሰከልክሙነ

- ሰከልክምዎ
- ሰከልክምዋ
- ሰከልክምዎሙ
- ሰከልክምዎን

አንትን

ሰከልክና

- ሰከልክናኒ
- ሰከልክናነ
- ሰከልክናሁ
- ሰከልክናሃ
- ሰከልክናሆሙ
- ሰከልክናሆን

ውእቱ
ሰከለ…

- ሰከለኒ
- ሰከለነ
- ሰከለከ
- ሰከለኪ
- ሰከለክሙ
- ሰከልክን
- ሰከሎ
- ሰከላ
- ሰከሎሙ
- ሰከሎን

ውእቱ
ሁለተኛ አካሄድ ሰከላ...

- ሰከላኒ
- ሰከላነ
- ሰከላከ
- ሰከላኪ
- ሰከላክሙ
- ሰከልላክን
- ሰከላሁ
- ሰከላሃ
- ሰከላሆሙ
- ሰከላሆን

ይእቲ
ሰከለተ...

- ሰከለትኒ
- ሰከለትነ
- ሰከለትከ
- ሰከለትኪ
- ሰከለትክሙ
- ሰከለትክን
- ሰከለቶ
- ሰከለታ
- ሰከለቶሙ
- ሰከለቶን

ውእቶሙ

ሰከሉ…

- ሰከሉኒ
- ሰከሉነ
- ሰከሉከ
- ሰከሉኪ
- ሰከሉክሙ
- ሰከሉክን
- ሰከልዎ
- ሰከልዋ
- ሰከልዎሙ
- ሰከልዎን

ውእቶን

ሰከላ…

- ሰከላኒ
- ሰከላነ
- ሰከላከ
- ሰከላኪ
- ሰከላክሙ
- ሰከላክን
- ሰከላሁ
- ሰከላሃ
- ሰከላሆሙ
- ሰከላሆን

የአእመረ ዝርዝር እርባታ

- አነ ስምንቱንም መራሕያን አስበ ሲነገር

<u>አነ ለአንተ/ቲ</u>

- አእመርኩከ/ኪ
- አአምረከ/ኪ
- ኣእምርከ/ኪ
- ኣእምርከ/ኪ

<u>አነ ለአንትሙ/ን</u>

- አእመርኩክሙ/ን
- አአምረክሙ
- ኣእምርክሙ/ን
- ኣእምርክሙ/ን

<u>አነ ለውእቱ/ይእቲ</u>

- አእመርክዎ/ዋ
- አአምሮ/ራ
- ኣእምሮ/ራ
- ኣእምሮ/ራ

<u>አነ ለውእቶሙ/ን</u>

- አእመርክዎሙ/ዎን
- አአምሮሙ/ን
- ኣእምሮሙ/ን
- ኣእምሮሙ/ን

- ንሕነ ስምንቱንም መራሕያን አሰቦ ሲነገር

<u>ንሕነ ለአንተ/ቲ</u>

- አእመርና(ነ)ከ/ኪ
- ነአመረከ/ኪ
- ናእመረከ/ኪ
- ናእመረከ/ኪ

<u>ንሕነ ለአንትሙ/ን</u>

- አእመርና(ነ)ክሙ/ን
- ነአመረክሙ/ን
- ናእመረክሙ/ን
- ናእመረክሙ/ን

ንሕነ ለውእቱ/ይእቲ

- አእመርናሆ(ናሁ)/ና(ናሃ)
- ነአምሮ/ራ
- ናእምሮ/ራ
- ናእምሮ/ራ

ንሕነ ለውእቶሙ/ን

- አእመርናሆሙ(ናሆሙ)/ሆን(ናሆን)
- ነአምሮሙ/ን
- ናእምሮሙ/ን
- ናእምሮሙ/ን

<u>እንተ ለውእቱ</u>	<u>እንተ ለውእቶሙ</u>	<u>እንተ ለውእቶን</u>	<u>እንተ ለይእቲ</u>	<u>እንተ ለአነ</u>	<u>እንተ ለንሕነ</u>
አእመርኮ	አእመርኮሙ	አእመርኮን	አእመርካ	አእመርከኒ	አእመርከነ
ተአምሮ	ተአምሮሙ	ተአምሮን	ተአምራ	ተአምረኒ	ተአምረነ
ታእምሮ	ታእምሮሙ	ታእምሮን	ታእምራ	ታእምረኒ	ታእምረነ
ኣእምሮ	ኣእምሮሙ	ኣእምሮን	ኣእምራ	ኣእምረኒ	ኣእምረነ

አንቲ ለውእቱ	አንቲ ለውእቶሙ	አንቲ ለውእቶን	አንቲ ለይእቲ	አንቲ ለአነ	አንቲ ለንሕነ
አእመርኪዮ	አእመርኪዮሙ	አእመርኪዮን	አእመርኪያ	አእመርክኒ	አእመርክነ
ተአምሪዮ/ርዮ	ተአምሪዮሙ/ርዮሙ	ተአምሪዮን/ርዮን	ተአምሪያ/ርያ	ተአምሪኒ/ርኒ	ተአምሪነ/ርነ
ታእምሪዮ/ርዮ	ታእምሪዮሙ/ርዮሙ	ታእምሪዮን/ርዮን	ታእምሪያ/ርያ	ታእምሪኒ/ርኒ	ታእምሪነ/ርነ
ኣእምሪዮ/ርዮ	ኣእምሪዮሙ/ርዮሙ	ኣእምሪዮን/ርዮን	ኣእምሪያ/ርያ	ኣእምሪኒ/ርኒ	ኣእምሪነ/ርነ

አንትሙ ለውእቱ	አንትሙ ለውእቶሙ	አንትሙ ለውእቶን	አንትሙ ለይእቲ	አንትሙ ለአነ	አንትሙ ለንሕነ
አእመርክምዎ	አእመርክምዎሙ	አእመርክምዎን	አእመርክምዋ	አእመርክሙኒ	አእመርክሙና
ተአምርዎ	ተአምርዎሙ	ተአምርዎን	ተአምርዋ	ተአምሩኒ	ተአምሩና
ቷእምርዎ	ቷእምርዎሙ	ቷእምርዎን	ቷእምርዋ	ቷእምሩኒ	ቷእምሩና
ኣእምርዎ	ኣእምርዎሙ	ኣእምርዎን	ኣእምርዋ	ኣእምሩኒ	ኣእምሩና

አንትን ለውእቱ	አንትን ለውእቶሙ	አንትን ለውእቶን	አንትን ለይእቲ	አንትን ለአነ	አንትን ለንሕነ
አእመርክናሁ	አእመርክናሆሙ	አእመርክናሆን	አእመርክናሃ	አእመርክናኒ	አእመርክናነ
ተአምራሁ	ተአምራሆሙ	ተአምራሆን	ተአምራሃ	ተአምራኒ	ተአምራነ
ቃእምራሁ	ቃእምራሆሙ	ቃእምራሆን	ቃእምራሃ	ቃእምራኒ	ቃእምራነ
ኣእምራሁ	ኣእምራሆሙ	ኣእምራሆን	ኣእምራሃ	ኣእምራኒ	ኣእምራነ

- ውእቱ አሥሩንም መራሕያን አስቦ ሲነገር

<u>ውእቱ ለአነ</u>

- አእመረኒ =አወቀኝ
- የአምረኒ =ያውቀኛል
- ያእምረኒ =ያውቀኝ ዘንድ
- ያእምረኒ =ይወቀኝ

<u>ውእቱ ለንሕነ</u>

- አእመረነ=አወቀን
- የአምረነ=ያውቀናል
- ያእምረነ=ያውቀን ዘንድ
- ያእምረነ=ይወቀን

<u>ውእቱ ለአንተ/ቲ</u>

- አእመረከ/ኪ =አወቀሽ
- የአምረከ/ኪ =ያውቅሻል
- ያእምርከ/ኪ=ያውቅሽ ዘንድ
- ያእምርከ/ኪ=ይወቅሽ

<u>ውእቱ ለአንትሙ/ን</u>

- አእመረክሙ/ን
- የአምረክሙ/ን
- ያእምርክሙ/ን
- ያእምርክሙ/ን

ውእቱ ለውእቱ/ይእቲ

- አእመሮ/ራ
- የአምሮ/ራ
- ያእምሮ/ራ
- ያእምሮ/ራ

ውእቱ ለውእቶሙ/ን

- አእመሮሙ/ን
- የአምሮሙ/
- ያእምሮሙ/ን
- ያእምሮሙ/ን

- ❑ይእቱ አሥሩንም መራሕያን አሰባ ስትነገር

<u>ይእቲ ለአነ/ለንሕነ</u>

- አእመረተኒ/ነ
- ተአምረኒ/ነ
- ታእምረኒ/ነ
- ታእምረኒ/ነ

<u>ይእቲ ለአንተ/ቲ</u>

- አእመረተከ/ኪ
- ተአምረከ/ኪ
- ታእምርከ/ኪ
- ታእምርከ/ኪ

<u>ይእቲ ለአንትሙ/ን</u>

- አእመረተክሙ/ን
- ተአምረክሙ/ን
- ታእምርክሙ/ን
- ታእምርክሙ/ን

ይእቲ ለውእቱ/ይእቲ

- አእመረቶ/ታ
- ተአምሮ/ራ
- ታእምሮ/ራ
- ታእምሮ/ራ

ይእቲ ለውእቶሙ/ን

- አእመረቶሙ/ን
- ተአምሮሙ/ን
- ታእምሮሙ/ን
- ታእምሮሙ/ን

ውእቶሙ አሥሩንም መራሕያን አሰበው ሲነገሩ

ውእቶሙ ለውእቱ	ውእቶሙ ለውእቶሙ	ውእቶሙ ለውእቶን	ውእቶሙ ለይእቲ	ውእቶሙ ለአንተ
አእመርዎ =አወቁት	አእመርዎሙ	አእመርዎን	አእመርዋ	አእመሩከ
የአምርዎ =ያውቁታል	የአምርዎሙ	የአምርዎን	የአምርዋ	የአምሩከ
ያእምርዎ =ያውቁት ዘንድ	ያእምርዎሙ	ያእምርዎን	ያእምርዋ	ያእምሩከ
ያእምርዎ =ይወቁት	ያእምርዎሙ	ያእምርዎን	ያእምርዋ	ያእምሩከ

ውእቶሙ ለአንትሙ	ውእቶሙ ለአንትን	ውእቶሙ ለአንቲ	ውእቶሙ ለአነ	ውእቶሙ ለንሕነ
አእመሩክሙ	አእመሩክን	አእመሩኪ	አእመሩኒ	አእመሩነ
የአምሩክሙ	የአምሩክን	የአምሩኪ	የአምሩኒ	የአምሩነ
ያእምሩክሙ	ያእምሩክን	ያእምሩኪ	ያእምሩኒ	ያእምሩነ
ያእምሩክሙ	ያእምሩክን	ያእምሩኪ	ያእምሩኒ	ያእምሩነ

ውእቶን አሥሩንም መራሕያን አስበው ሲነገሩ

ውእቶን ለውእቱ	ውእቶን ለውእቶሙ	ውእቶን ለውእቶን	ውእቶን ለይእቲ	ውእቶን ለአንተ
አእመራሁ =አወቁት	አእመራሆሙ	አእመራሆን	አእመራሃ	አእመራከ
የአመራሁ=ያውቁታል	የአመራሆሙ	የአመራሆን	የአመራሃ	የአመራከ
ያእምራሁ =ያውቁት ዘንድ	ያእምራሆሙ	ያእምራሆን	ያእምራሃ	ያእምራከ
ያእምራሁ =ይወቁት	ያእምራሆሙ	ያእምራሆን	ያእምራሃ	ያእምራከ

ውእቶን ለአንትሙ	ውእቶን ለአንትን	ውእቶን ለአንቲ	ውእቶን ለአነ	ውእቶን ለንሕነ
አእመራክሙ	አእመራክን	አእመራኪ	አእመራኒ	አእመራነ
የአመራክሙ	የአመራክን	የአመራኪ	የአመራኒ	የአመራነ
ያእምራክሙ	ያእምራክን	ያእምራኪ	ያእምራኒ	ያእምራነ
ያእምራክሙ	ያእምራክን	ያእምራኪ	ያእምራኒ	ያእምራነ

አእሚሮ=አውቆ

፩ ውእቱ ተብዬ አሥሩን መራሕያን ሲያውቃቸው

አነ= አእሚሮኒ(አውቆኝ)

ንሕነ=አእሚሮነ(አውቆን)

አንተ= አእሚሮከ(አውቆህ)

አንቲ=አእሚሮኪ(አውቆሽ)

አንትሙ=አእሚሮክሙ(አውቋችሁ)

አንትን= አእሚሮክን(አውቋችሁ)

ውእቱ= አእሚሮሁ(አውቆት)

ይእቲ=አእሚሮሃ(አውቋት)

ውእቶሙ=አእሚሮሆሙ(አውቋቸው)

ውእቶን= አእሚሮሆን(አውቋቸው)

የቀሩትን እና ሌሎቹንም መራህያን እንዲህ እያደረጉነው የሚረባው።

ጥቁ እሴብሕ!!!